# የ1ኛ ቆሮንቶስ ጥናት(30)

## ጥናት አንድ ሐዋ ሥራ 18፡1-28

የጥናት ዓላማ፡- ከርኩሰትና ከሃጥያት መብዛት የተነሳ የእግዚአብሄር ጉባኤ መስሎ በማይታየው ጉባኤ መሃል እንኳን እግዚአብሄር ለራሱ መንግሥት የመረጣቸው ሰዎች እንዳሉ መዘንጋት እንደማይገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡-‹‹ጌታም ሌሊት በራዕይ ጳውሎስን እንዲህ አለው፤ አትፍራ፣ ተናገር፣ ዝምም አትበል…በዚች ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና፡፡›› ሥራ 18፡9-10

1. የሐዋ ሥራ 18፡1-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ‹‹ከዚህ በኋላ የሚለው የሚጠቁመው ወደየትኛው ሃሳብ ነው? ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ በመጀመሪያ ያገኛቸው ሰዎች እነማን ናቸው? ስለእነዚህ ወደ ቆሮንቶስ አገባብ ሁኔታ የምናውቀው ነገር ምንድነው?
2. በዚህ ምንባብ መሰረት የጳውሎስ አገልግሎት ሲላስና ጢሞቲዎስ ከመምጣታቸው በፊትና በኋላ ምን ልዩነት ይታይሃል? ጳውሎስ ለአይሁድ ባደረገው አገልግሎት የመልዕክቱ ትኩረት ምን ነበረ? ለምን?
3. አይሁድ ጳውሎስ ለሰበከው የወንጌል መልዕክት የሰጡት ምላሽ ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ፡፡ ጳውሎስ ለምላሻቸው በእርሱ በኩል የወሰደው እርምጃስ ምን ነበረ? ከዚህ ለራስህ ምን ትማራለህ?
4. በቁ6 ላይ የሃይማኖት ሰዎች፣ በቁ8 ላይ ደግሞ ሃጥያተኞች የተባሉት አህዛብ ለወንጌል ያሳዩትን ምላሽ እናያለን፡፡ ከዚህ ምን ልንማር እንደምንችል ተናገር፡፡
5. በቁ9-11 ላይ እግዚአብሄር ስለ ቆሮንቶስ ከተማ ለጳውሎስ የገለጠለት አንድ እውነት ምንድነው? ይህንንስ አስመልክቶ እግዚአብሄር ለባሪያው የተናገራቸው ማበረታቻዎችና እንዲሁም የተስፋ ቃል ምን እንደሆነ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ዓውደ ምንባቡን በማጤን ጳውሎስ አንድ ዓመት ተኩል ያህል በቆሮንቶስ ለመቀመጥ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
6. እግዚአብሄር ብዙ ሰዎች በቆሮንቶሰ ከተማ አሉኝ ካላቸው መሃል የምናውቃቸው እነማን ይገኙበታል?
7. በቁ17 ላይ የምናየው ሶስቴንስ ስለ ተባለው ሰው 1ኛ ቆሮ 1፡1 ምን ተጨማሪ ሃሳብ ይሰጠናል? በቁ24-25 ላይ አጵሎስ ስለሚባለው ወንድም ምን እንመለከታለን? ቁ26 ላይስ ስላሉት ጵርስቅላና አቂላ ምን መረዳት እንችላለን?
8. በዚህ ክፍል ያየናቸው ወገኖች ሁሉ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚገኙ ከሆነ ለምንድነው ቤተ ክርስትያኒቱ መጥፎ ስም የተሰጣት? በ1ኛ ቆሮ 1፡2 የእግዚአብሄር ቤተ ክርስትያን በመባል ስጥጠራ፤ በሥራ 18፡10 ደግሞ ብዙዎቹ የጌታ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በርኩሰት የሚመላስ ቁጥሩ መብዛቱ ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሄር መሆኗን ይቀይራል ብለህ ታምናለህ?፤ ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ብዙ አመጻና ርኩሰት ቢታይም ቆሮንቶስን እንዳጠራ እግዚአብሄር ቤቱን የሚያጠራበት ጊዜ አለውና ተስፋ አትቁረጥ፡፡

# ጥናት ሁለት 1ኛ ቆሮ 1፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- በቤተ ክርስትያን ውስጥ ችግር በሚኖርበት ወቅት፤ ወሬን ለወሬነቱ ያህል የምናወራ ሰዎች እንዳንሆንና፤ እግዚአብሄርን ለሚፈሩ፣ ለቤተክርስትያን ለሚቆረቆሩ በጸሎትም ሆነ በሚችሉት መንገድ ሁሉ መፍትሄ ለማማምጣት ለሚችሉ ሰዎች መናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡-‹‹ወንድሞች ሆይ፤ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ከቀሌዔ ቤተሰብ ሰምቻለሁ፤ ነገሩም እንዲህ ነው፤ ከእናንተ አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ ሲል ሌላው…እኔስ የክርስቶስ ነኝ ይላል፡፡›› 1ኛ ቆሮ 1፡17

1. 1ኛ ቆሮ 1፡1-17 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ጳውሎስ ስለራሱ ማንነት ምን ይነግረናል? የእርሱ ጥሪ ያ ከሆን ስለራስህ ጥሪስ ምን መናገር ትችላለህ? በዚህ ክፍል ስናይ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ባለቤት ማነው?
2. ቁ2 ላይ ‹‹በቆሮንቶስ ላለችው›› የሚለውና ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ሆነው ከሚጠሩት…›› የሚሉት ሁለት ስንኞች ስለ ቤተ ክርስትያን ማንነት ምን መረዳት ትችላለህ?
3. ቁ8-9 ላይ እግዚአብሄር በእነዚህ ቅዱሳን ህይወት ሊሰራ ስላለው ነገር የሚናገረው እውነት ምንድነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሄር ታማኝነት የተናገረበት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. እግዚአብሄር በቁ9 ላይ ቅዱሳኑን ወደየት እንደጠራ ነው የምናየው? 1ኛ ዮሐ 1፡3 ማየት ይረዳል፡፡ የቆሮንቶስ ሰዎች የጥሪውን ምንነት በትክክል አልተረዱትም ሊያሰኘን የሚችል ምን ሃሳብ ታያለህ? ዛሬስ በዘመናችን የሚታየው ችግር በቆሮንቶስ ከሚታየው የተለየ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
5. ጳውሎስ በቁ10 ላይ ‹‹አንድ ሃሳብ እንዲኖራችሁ›› ይላቸዋል፡፡ ይህ ማለት የቤተ ክርስትያኒቱ ሰዎች ሁሉ አንድ ነገር እንዲያስቡ ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው? ፊሊ 2፡2-5 ተመልከት፡፡
6. በዚህ ምንባብ ውስጥ ለመከፋፈያ የተጠቀሙባቸው ስሞች ማን ማን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ከነዚህ ቡድኖች መሃል በአሸናፊነት የተጠቀሰ ታያለህ ወይ? ለምን?
7. በቁ13 ላይ የቆሮንቶስ ሰዎች የተጠየቋቸው ሶስት ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው? በነዚህ ጥያቄዎች በመነሳት ጳውሎስ ሊያስተምራቸው ያሰበው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ጳውሎስ በቁ17 ላይ ‹‹ክርስቶስ የላከኝ ወንጌልን እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም›› ማለቱ ጥምቀት አያስፈልግም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው?
8. የቆሮንቶስን ችግር ለመፍታት ከጳውሎስ ሌላ እግዚአብሄር የተጠቀመበት ሰው ማነው ትላለህ? ለምን ይህን ማለት ቻልክ? ቤተ ክርስትያን በዚህ ሁኔታ ስትገኝ የአንተ ተሳትፎ ምን መሆን አለበት ብለህ ታምናለህ? የቤተ ክርስትያንን ችግር እግዚአብሄርን ለሚፈሩ፣ ለቤተ ክርስትያን ለሚቆረቆሩ፣ በጸሎት ሆነ በሚችሉት ሁሉ መፍትሄን ለመፈለግ ለሚጥሩ ሰዎች መናገር እግዚአብሄር በመፍትሄነት ሊጠቀምበት ስለሚችል ወሬህን ለማን እንደምታወራ ልትጠነቀቅ ይገባሃል፡፡

# ጥናት ሶስት 1ኛ ቆሮ 1፡18-31

የጥናት ዓላማ፦ የወንጌል አግልጋይ የሆነ ሰው፤ ትኩረቱ ሰዎች መስማት ወይም ማየት በሚፈልጉትን ነገር ላይ ሳይሆን ሊያድናቸው በሚችለው በተሰቀለው ክርስቶስ ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፡፡›› 1ኛ ቆሮ 1፡22-23

1. 1ኛ ቆሮ 1፡18-31 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ18 ላይ የመስቀሉን ቃል አስመልክቶ ስንት ዓይነት ሰዎችን ታያለህ? እነዚህ እነማን ናቸው? እነዚህ ሰዎች እያንዳንዳቸው ለመስቀሉ ቃል ምላሻቸው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
2. ቁ18-25ትን ስትመለከት በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ምን ቃል ታያለህ? ይህ ቃል በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ እንደተጠቀሰ ተናገር፡፡ የዚህ ቃል ሁለቱ ምንጮች ምንና ምንድናቸው?
3. በቁ20-21 ላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ዘርዝር፡፡ ይህ ማለት በዓለም ላይ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የሉም ለማለት ነው ወይስ ምን ማለቱ ነው?
4. ማቴ 11፡25 ላይ ያለው ክፍል እግዚአብሄር ደህንነትን ከአንዳንዶች ሰውሮ ለሌሎች መግለጡ ጥያቄ ለሚሆንባቸው ሰዎች በቁ20-25 ላይ ያለው ሃሳብ መልስ የሚሆነው በምን መንገድ ነው? ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም አስመልክቶ ከዚህ ምን መማር እንችላለን?
5. የተወሰኑ ቁጥሮችን ለጊዘው በመዝለል ከቁ26-31 ያለው ምንባብ በድጋሚ ይነበብ፡፡ በቁ 26-29 ላይ የቆሮንቶስ አማኞች ስለ ማንነታቸው እንዲያስታውሱ የሚጠይቃቸው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር ስለ ሰራውስ ነገር ምን ያሳያቸዋል? ለምንድነው እግዚአብሄር ይህንን ማድረግ የወሰነው ይላቸዋል?
6. ቁ30-31 አማኝ ከእግዚአብሄር ጋራ ላለው ህይወት፤ ከክርስቶስ ሌላ ተጨማሪ ነገር የማያስፈልገው መሆኑን የሚያስተምረን በምን መንገድ ነው? ላንተ ህይወትስ ክርስቶስ ሙላትህ እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ታየዋለህ ወይ?
7. ወደ ቁ22-25 እንመለስና በተለይም በቁ23ና 24 ላይ የምናያቸው ሶስት ዓይነት ሰዎች ማን ማን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ከእነዚህ ሶስት ዓይነት ሰዎች ሁለቱ ጥያቄና መሻት እንዳላቸው ይናገራል፡፡ እያንዳንዳቸው የሚሹት ወይም ማየት የሚፈልጉት ነገር ምንድነው?
8. በቁ22 ላይ ሰዎቹ ይሻሉ ወይም ይፈልጋሉ የተባለውን ነገር አግኝተዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ተናገር፡፡ የተሰቀለው ክርስቶስ በእነዚህ ሶስት ሰዎች ዓይን የሚታየው በምን መንገድ ነው? ሰዎች መስማትና ማየት የሚፈልጉትን ሳይሆን የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ መስበክ ብቸኛ መንገድ መሆኑን አትርሳ፡፡

# ጥናት አራት 1ኛ ቆሮ 2፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- መንፈስ ቅዱስ አጽናኝና በአዲስ ቋንቋ ለመናገር የሚያስችለን ብቻ ሳይሆን ያለ እርሱ ደህንነት የሚባል ነገር ሊኖር እንደማይችል ተረድተን ለእርሱ ተገቢውን ምስጋናና አክብሮት ለማበርከት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚህ ዓለም ገዢዎች አንዳቸውም ይህንን ጥበብ አልተረዱትም… እግዚአብሄር ግን ይህንን በመንፈሱ አማካኝነት ለእኛ ገልጦልናል፡፡›› 1ኛ ቆሮ 2፡8-10

1. 1ኛ ቆሮ 2፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ 2፡1-5 ላይ ሰንት ዓይነት ወንጌልን የመስበኪያ መንገዶች ማየት ትችላለህ? ጳውሎስ መጠቀም የወሰነው የትኛውን መንገድ ነው? ለምን?
2. በነዚህ በመጀመሪያዎቹ አምስት ጥቅሶች ውስጥ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 1፡31 ላይ ‹‹የሚመካ በጌታ ይመካ፡፡›› የሚለውን መርሆ በህይወቱ ተፈጻሚ አድርጎታል የሚያሰኘን የትኛው ሃሳብ ነው?
3. 2፡6-9 ላይ የምናያቸው ሁለት የጥበብ ዓይነቶች ምንና ምንድናቸው? ይህ ክፍል በተለይ ስለ እግዚአብሄር ጥበብ የሚናገራቸውን ሃሳቦች በሙሉ አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
4. በቁ1 ላይ ጳውሎስ በሚያናግራቸው ሰዎችና በቁ 6 ላይ በሚያናግራቸው ሰዎች መሃል የምታየው ልዩነት አለ ወይ? አለ የምትል ከሆነ ልዩነቱ ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
5. ቁ2፡10-13 በነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ በብዛት የተጠቀሰው ቃል ምንድነው? ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? ይህንን ቃል የተጠቀመባቸው መንገዶች ስንት ናቸው? ዘርዝራቸው፡፡
6. ጳውሎስ በ2፡14-16 ላይ ሰዎችን በስንት ከፍሎ ነው የሚያየው? እነዚህ ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ፍጥረታዊ ሰው የማይችላቸው በማለት የተናገራቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
7. አጠቃለን ምዕራፉን ስንመለከት፤ ሁለት የስብከት መንገዶች(ቁ1-5)፣ ሁለት ዓይነት ጥበብ(ቁ6-9)፣ ሶስት ዓይነት መንፈስ(ቁ10-13) እና ሁለት ዓይነት ሰዎች(14-16) በማለት የተመለከትናቸውን ለማስታወስ እንዲረዳን እንደገና በመዘርዘር ተናገር፡፡
8. ቁ4፣ ቁ10፣ ቁ12 እና ቁ13ትን ስናነብ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ደህንነት መቀበልና እንዲሁም ከደህንነትም ባሻገር በህይወታቸው ስላለው አስተዋጽዖ እነዚህ ክፍሎች ምን ያስረዱናል? ሰፋ አድርጋችሁ ተወያዩበት፡፡
9. ያለ መንፈስ ቅዱስ ደህንነት ሊኖር አይችልም በሚለው ሃሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? ለምን? እኛ ከምናስበው በላይ መንፈስ ቅዱስ በደህንነታችን ላይ ይህ ነው የማይባል አስተዋጽዖ ስላለውና ያለ እርሱ ደህንነት ሊኖር ስለማይችል ተገቢውን ምስጋናና አምልኮ የመስጠት ልምድ በማዳበር በተለይም በፊታችን ባለው ሳምንት ሥራዩ ብለህ ተለማመደው፡፡

# ጥናት አምስት 1ኛ ቆሮ 3፡1-9

የጥናት ዓላማ፡- ከጌታ የምንቀበለው የአገልግሎት ሽልማት የሚወሰነው በአገልግሎታችን አይነት ወይም ምንነት ሳይሆን፤ ከእርሱ የተቀበልነውን መክሊት በትጋትና በታማኝነት በመሥራታችን መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የሚተክልም ሆነ የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የራሱን ሽልማት ይቀበላል፡፡›› 1 ቆሮ 3፡8

1. 1ኛ ቆሮ 3፡1-9 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተክርስትያን ለማገልገል የነበረበት ችግር ምን ነበረ? ይህ ችግር አለመዳናቸውን ያረጋግጣል በሚለው አባባል ትስማማለህ ወይ? ለምን?
2. በቁ2 ላይ የምንመለከታቸው የምግብ ዓይነቶች ምንና ምንድናቸው? እንደ እረኛ የእድገት ደረጃቸውን ለይቶ ማወቁ ስለጳውሎስ አገልግሎት ጠቃሚ የሚሆነው በምን መንገድ ነው?
3. በቁ3-4 መሰረት የቆሮንቶስ አማኞች ከህጻንነት ባሻገር የነበረባቸው ሌላ ችግር ምን ነበረ? በዚህ ክፍል ውስጥ የስጋዊነት መለያ ወይም ፍሬ ሆነው የተጠቀሱት ነገሮች ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ የነዚህን ሁለት ነገሮች ምንነት በጥልቀት ተነጋገሩባቸው፡፡
4. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ እንደ ቅንዓትና ክርክር የመሰሉትን ነገሮች መለማመድ ተግባራችን ካላመኑ ሰዎች የተለየ እንዳልሆነ የሚጠቁሙን ሁለት ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
5. ከላይ በተመለከትናቸው አራት ቁጥሮች መሰረት የአማኞችን መንፈሳዊ ማንነት ለመግለጽ መጠቀም የምንችልባቸው በሙሉ ዘርዝር፡፡ ከነዚህ ሁሉ ራስህን በየትኛው ውስጥ ታገኛለህ?
6. ቁ1-4 ያተኮረባቸው ሰዎችና ቁ5-9 ያተኮረባቸው እነማን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ቁ5-9ትን ስናነብ ለቆሮንቶስ አማኞች እድገት እየሰሩ ያሉ እነማን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ከአገልጋዮቹ ሁሉ የበላይነቱን ሥፍራ የተሰጠው ለማን ነው? ለምን?
7. ጳውሎስ ስለአጵሎስና ስለራሱ አገልግሎት ስለነበረው አመለካከት የሰነዘራቸውን ሃሳቦች በሙሉ በዝርዝር ተናገር፡፡ የአንዳችን አገልግሎት ከሌላችን ምንም ዓይነት ብልጫ እንደሌለው መረዳት ምን ጥቅም አለው ብለህ ታምናለህ?
8. ቁ8 ‹‹እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የራሱን ሽልማት ይቀበላል፡፡›› ከዚህ አነጋገር አገልግሎትን አስመልክቶ የምንረዳቸው እውነቶች ምንድናቸው? ለምንድነው ሽልማቱ እንደ ሥራው ‹‹መጠን›› እንጂ እንደ ሥራው ‹‹ዓይነት›› ያልሆነበት ምክንያት? በአገልግሎትህ ሥምና ዓይነት ሳይሆን ለጌታ ምን ያህል በትጋትና በታማኝነት የመሥራት ጉዳይ ስለሆነ በተሰጠህ መክሊት ተግተህ ሥራበት፡፡

# ጥናት ስድስት 1ኛ ቆሮ 3፡10-23

የጥናት ዓላማ፡- በእርሱ ውስጥ ስንኖር፤ እኛ የክርስቶስ ክርስቶስም የእኛ ከመሆኑ በተጨማሪ እኛ ለእያንዳንዱ አማኝ እያንዳንዱ አማኝ ደግሞ ለእኛ በረከት ሆኖ የተሰጠን መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አለምም ሆነ ህይወት ወይም ሞት፤ አሁን ያለውም ሆነ ወደፊት የሚመጣው፤ ሁሉ የእናንተ ነው፤ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስቶስም የእግዚአብሄር ነው፡፡›› 1ኛ ቆሮ 3፡22-23

1. 1ኛ ቆሮ 3፡10-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ1፡9 ላይ እኛ የእግዚአብሄር እርሻና ህንጻ እንደሆንን ይናገራል፡፡ ጳውሎስ በእርሻው ላይና እንዲሁም በህጻው ላይ የነበረው የአገልግሎት ድርሻ ምን እንደነበረ ተናገር፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ተመሳሳይነት አላቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡
2. 3፡7 ላይ ከሚናገረው አነጋገርና በቁ 10 ላይ ‹‹በተሰጠኝ ጸጋ መጠን›› ከሚለው አነጋገሩ ጳውሎስ እያገለገለ ስላለው አገልግሎት ስለለው አመለካከት ምን መገምገም እንችላለን? በዚሁ በቁ10 ላይ የግንባታው ሥራ የማን ነው? ከግንባታ አኳያ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
3. በቁ11 ላይ ድጋሚ መሰረት መጣል ያላስፈለገው ለምንድነው? ድጋሚ መሰረት መጣል አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? ቁ12-13 ትን ስንመለከት በተመሰረተው መሰረት ላይ ሰው ሊገነባ የሚችልባቸው ስንት የግንባታ መሳሪያዎችን ታያለህ? ዘርዝራቸው፡፡
4. ቁ13-15 ያለው ክፍል አገልግሎትን አስመልክቶ የሚነግረንን ቢያንስ አራት ሃሳቦችን በቅደም ተከተል ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ሥራው ከሰውየው ተለይቶ መታየቱ ምን ያስተምረናል?
5. ቁ16-17ትን ስናነብ በብዛት ተደጋግመው የተጠቀሱት ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው? በሁለቱ ቁጥሮች ውስጥ እነዚህ ቃላት ስንት ጊዜ ተደጋግመው ተጠቅሰዋል?
6. 1ኛ ቆሮ 6፡19፣ 1ኛ ቆሮ 3፡16 ንና ኤፌ 2፡19-20 በማንበብ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ የሚለውን ሃሳብ ጳውሎስ በስንት ዓይነት መንገድ ሲጠቀም ታያለህ? ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
7. በቁ12-17 ላይ ግንባታን አስመልክቶ ስንት አይነት ሰዎችን ይታዩሃል? ዘርዝራቸው፡፡ በዚሁ ምንባብ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን እግዚአብሄርነት የሚጠቁም ሃሳብ ታያለህ ወይ? የሚታይህ ከሆነ ለወገኖች የቱ እንደሆነ በመጠቆም አስረዳ፡፡
8. ‹‹እናንተም የክርስቶስ ናችሁ›› ሲል የሚያጠቃልለው እነማንን ነው? ይህ አነጋገር ከቁ1፡12 ጋራ የሚቃረነው በምን መንገድ ነው?
9. ቁ21-23 ላይ እግዚአብሄር ለአማኝ የሰጣቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር፡፡ ይህ ሁሉ በረከት ተሰጥቶን አንድ ሰው ላይ ብቻ ማተኮር ጉዳቱ ምን ይመስልሃል? እያንዳንዳችን ለእያንዳንዳችን የተሰጠን በረከቶች መሆናችንን በማስተዋል ለመመላለስ ጌታ ይርዳን፡፡

# ጥናት ሰባት 1ኛ ቆሮ 4፡1-7

የጥናት ዓላማ፡- በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እርስ በእርሳችን ልንፈራረድ የምንችልባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ብናይም፤ የሰዎችን አስተሳሰብና በልብ ውስጥ ባለው ነገር ግን ፍርድ የጌታ ብቻ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…በምንም ነገር አትፍረዱ፤ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ፡፡ እርሱ በጨለማ ውስጥ የተሰወረውን ወደ ብርሃን ያወጣዋል፤ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውንም ሃሳብ ይገልጠዋል፡፡ 1ኛ ቆሮ 4፡5

1. 1ኛ ቆሮ 4፡1-7 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ እኛ በማለት ጸሐፊው የሚናገረው እነማንን ነው? የአገልጋይ ሁለት መለያ ሆነው በዚህ ቁጥር ውስጥ የተነገሩት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ ቁጥር በ1ኛ ቆሮ 3፡22 ላይ የተናገረውን ሃሳብ በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱት የሚጠቅመው እንዴት ይመስልሃል?
2. ቁ1 መልዕክቱን የሚናገረው ለማን ነው? ቁ2 ትስ ትኩረቱ ማን ላይ ነው? ከባለ አደራውዎች ስለሚጠበቀው ነገር ጸሐፊው ምን ይናገራል? በተለይ ይህንን ሲል ከምን አንጻር ይመስልሃል?
3. በቁ3-5 ውስጥ በብዛት ተደጋግሞ የሚታየው አንድ ሃሳብ/ቃል ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል በጳውሎስ ላይ ስለመፍረድ አስመልክቶ የተጠቀሱትን አራቱን ሰዎች ዘርዝር፡፡ ጳውሎስ በእርሱ ላይ ለመፍረድ ብቃት አለው ብሎ የሚያምነው ማንን ነው? ለምን?
4. ለምንድነው ጳውሎስ በራሱ ላይ መፍረድ እንኳን የማይችልበት ምክንያት? ቁ4 ስለ ህሊና የሚያስተምረን አንድ ትልቅ እውነት ምንድነው?
5. 1ኛ ቆሮ 5፡12፣ 6፡2-5፣ 10፡15 ትን በማንበብ እነዚህ ቁጥሮች በሰው ላይ ስለመፍረድ ምን እንደሚናገሩ ሃሳብህን ስጥ፡፡ እነዚህን ምንባቦች በዛሬው ምንባብ ውስጥ ከተመለከትነው የፍርድ ዓይነት የሚለያቸው ነገር ምን ይመስልሃል?
6. ሰዎችን በሌሎች ላይ መፍረድ እንዳይችሉ የሚያግዷቸው በቁ5 ላይ የተጠቀሱት ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? እንደነዚህ ያሉ ነገሮች ፍርዳቸው መቼ ነው? ቁ5 ላይ ››የሚገባውን›› የሚለው ሃሳብ እኛ ብንፈርድ ልንሰጥ ስለምንችለው ብያኔ ምን ይጠቁመናል?
7. ጸሐፊው በቁ6 ላይ የራሱንና ፣ የኬፋን ምናልባትም የጴጥሮስንና የኢየሱስንም ስም ጭምር የተጠቀምኩበት ምክንያት ለምንድነው ይላል? ስማቸውን የተጠቀመው ሰዎች ለምሳሌነት እንዲያገለግሉ እንጂ መከፋፈሉ በእነርሱ ስም ላይሆን ይችላል ስለሚለው ሃሳብ ምን ታስባህ? መከፋፈልን አስመልክቶ ሃሳቡን ያጠቃለለበትን አረፍተ ነገር ተናገር፡፡
8. በተራ ቁጥር 5 ላይ በተነጋገርነው መነጽር በማየት መፍረድ የምንችልባቸውን ሁኔታዎች የሚያሳዩ ሁለትና መፍረድ የማንችልባቸው ደግሞ ሁለት በማንሳት በስፋት ተወያዩባቸው፡፡ መፍረድ ያልነበረብህ የፈረድክበት፣ መፍረድ ሲገባህ ሳትፈርድ ያለፍክበት ሁኔታ ካለ ለወገኖች ተናገር፡፡ መቼ መፍረድና መቼ አለመፍረድ እንደሚገባችሁ እንድታውቁ ጌታ ጥበብን እንዲሰጣችሁ በመዚጊያ ጸሎታችሁ እንዲሁም በሳምንቱ የግል ጸሎት ጊዜያችሁ ጸልዩ፡፡

## ጥናት ስምንት 1ኛ ቆሮ 4፡8-21

የጥናት ዓላማ፡- በድፍረት እኔን የምትመስሉ ሁኑ በማለት አፍን ሞልቶ ለመናገር የሚቻለው፤ የምንናገረው ወይም የምናስተምረው ትምህርትና አረማመዳችን የሚጣጣም ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ እኔን እንድትመስሉ እለምናችኋለሁ…እርሱም በየስፍራው በሚገኙ አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ከማስተምረው ትምህርት የሚስማማውን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የህይወት አካሄዴን ያሳስባችኋል፡፡›› 1ኛ ቆሮ 4፡16-17

1. 1ኛ ቆሮ 4፡8-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ8 ትን ስታነብ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለራሳቸው ስላላቸው  አመለካከት ምን ትረዳለህ? በቁ7 ላይ ጳውሎስ የጠየቃቸው ጥያቄዎች በቁ8 ላይ የተመለከትናቸውን ሰዎች እንዴት እንደሚመለከታቸው አስረዳ፡፡
2. ቁ9-10 ርን በማንበብ ጳውሎስ አንዳንዴ ስለሚሰማው ስሜት በተለይ በቁ9 ላይ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው? ሐዋርያቱን ከቆሮንቶስ አማኞች ጋራ ያነጻጸረባቸው ሶስቱ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
3. ቁ11-12 ላይ ጳውሎስ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በህይወቱ የሚያልፉ የዘረዘራቸው ስድስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ሃብትና ባለጠግነት የክርስትያን መብቱ እንደሆነና እግዚአብሄርን መምሰል ማትረፊያ እንደሆነ ለሚናገሩ ሰዎች ይህ ክፍል በምን መንገድ መልስ ይሆናል ብለህ ታምናለህ?
4. ጳውሎስ በቁ12-13 ከሰዎች ለሚደርስባቸው ነገሮች ስለምላሻቸው የሚናገረው ነገር ምንድነው? ከዚህ አኳያ ሉቃ 6፡28፣ ሮሜ 12፡14 ትና፣ 1ኛ ጴጥ 3፡9ን በማንበብ ስለ ሐዋርያቱ ምላሽ ምን መናገር ትችላለህ?
5. በጥያቄ ተራ ቁጥር 4 ላይ የደረሰባቸውን ክፉ ነገር ሁሉ እንደ እግዚአብሄር ቃል ማስተናገዳቸው ሁኔታቸውን እንደቀየረው ታያለህ ወይ? አስረዳ፡፡ እግዚአብሄርን በመታዘዛችንና ሁኔታዎቻችን በመቀየራቸው መሃል ስላለው ግንኙነት ይህ ክፍል የሚያስተምርህ እውነት ምንድነው?
6. ቁ14-16 ትን ስናነብ በሐዋርያው ጳውሎስና በቆሮንቶስ ሰዎች መሃል ስላለው ግንኙነት ምን እንረዳለን? ይህ ግንኙነት የተፈጠረው በምን አማካኝነት ነው? ከዚህ ግንኙነታቸው በመነሳት በዚህ ክፍል ጳውሎስ የሚያበረታታቸው ምን እንዲያደርጉ ነው?
7. በቁ17 ስለ ጢሞቲዎስ የሚናገራቸው መለያዎች ምን ምንድናቸው? ይህ ቁጥር ጢሞቲዎስ ወደ ቆሮንቶስ ስለተላከበት ምክንያት ምን ይነግረናል? በዚህ ክፍል መሰረት የጳውሎስን አገልግሎት ሃይል የሚሰጠው ነገር ምንድነው ትላለህ?
8. ቁ18-21 ይህ ክፍል ዋነኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚናገረው ስለምን ዓይነት ሰዎች ነው? 1ኛ ተሰ 1፡5ትን በማንበብ ይህ በቁ20 ላይ ሃይል የሚለው ምን ሊሆን እንደሚችል ተናገር፡፡
9. ለእነዚህ አማኞች እዚህ ካየናቸው ሰዎች ይልቅ ጳውሎስን መምሰል የሚኖርባቸው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ምሳሌዎችህ የቃልና የህይወት ሰዎች ናቸው ወይ? ወሬ ብቻ እንጂ የወንጌል ፍሬ በህይወታቸው የማይታይ ሰዎች ምሳሌያችን እንዳናደርግ ልንጠበቅ ያገባናል፡፡

# ጥናት ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 5፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር እንደ ንጉሥ ቂሮስ የመሳሰሉትን ነገሥታት ፈቃዱን ማከናወኛ አድርጎ መጠቀም ከመቻል አልፎ ከፈለገ ሰይጣንን እንኳን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ፈቃዱን እንዲፈጽም ማድረግ የሚችል አምላክ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹… *ሥጋው ጠፍቶ መንፈሱ በጌታ ቀን ትድን ዘንድ፤ እንደዚህ ዓይነቱ ለሰይጣን ይሰጥ፡፡*›› 1ኛ ቆሮ 5፡5

1. 1ኛ ቆሮ 5፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ላይ ‹‹የዝሙት እርኩሰት እንዳለ›› የሚለው አነጋገር ስለ ሁኔታው ሃላፊነት ወይም እየቀጠለ ያለ ስለመሆኑ ምን ይጠቁመናል? በመሃላቸው የሚካሄደውን  የዚህን ሃጥያት ክብደቱ ሊያሳየን የተጠቀመበት ሃሳብ የትኛው ነው?
2. የቆሮንቶስ ሰዎች ለምንድነው ሐዘን ሊሰማቸው ይገባ የነበረው?
3. ይህ በቁ4-5 ላይ የምናየው ስብሰባ እነማንን የሚያጠቃልል ነው? ማቴ 18፡15-17 ጌታ በሰጠን መመሪያ ውስጥ ይህ ሁኔታ የትኛው ደረጃ ላይ የደረሰ ይመስልሃል? ለምን ይህንን ማለት እንደቻክ አስረዳ፡፡
4. በዚህ ስብሰባ ላይ የሚሳተፉት አማኞች ሊወስዱት የሚገባቸው ቆራጥና ጠንካራ እርምጃ ምንድነው? የዚህን አይነት ጨካኞች ሊያሰኛቸው የሚችለውን አይነት እርምጃ መውሰዳቸው ዋነኛ ግቡ ምንድነው ትላለህ? ውሳኔያቸው ተግባራዊ እንደሚሆን እርግጠኛነት የሚሰጣቸው ነገር ምንድነው?
5. በቁ6-8 ላይ የዚህ አይነቱ ጠንካራ እርምጃ ለመወሰዱ ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል አነጋገር እርሾ የምን ምልክት ነው? በቁ7 ውስጥ ያለ እርሾ መሆን የሚኖርብን ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነገር ምንድነው?
6. ቁ9-11 ደግሞ ለተወሰደው እርምጃ የተሰጠው ሁለተኛው ምክንያት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ቀድሞ የጻፈላቸውን መልዕክት በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱት ማብራሪያ የሰጠበት ርዕስ ምን ነበረ?
7. ለምንድነው እርሱ በቁ11 ላይ ‹‹ወንድም ነኝ እያለ›› ሌሎች ወንድማችን ለማለት የሚቸገሩት?  ወንድምነቱን ወይም ክርስትናውን ለመመስከር የሚያስቸግር ሰው ገጥሞህ ያውቃል ወይ? እንደዚህ እንዲሰማህ የሆነበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?
8. ቁ12-13 ላይ ፍርድን አስመልክቶ ሰዎችን በስንት ዓይነት ይከፍላቸዋል? በቁ2፣ ቁ4 እና በቁ13 ላይ ከመሃላቸው እንዲወገድ የተነገራቸው ሰው ከየትኛው ክፍል ውስጥ ነው?
9. የቆሮንቶስ አማኞች የሚወስኑትን ውሳኔ ተፈጻሚ ማድረግን አስመልክቶ የሰይጣን አስተዋጽዖ ምንድነው? ኢዮብ 2፡6፣ 2ኛ ቆሮ 12፡7 ንና እንዲሁም በዛሬው ጥናት ቁ5ትን በማየት በእግዚአብሄርና በሰይጣን መሃል ስላለው ግንኙነት ምን ትማራለህ? ሰይጣንን እንኳን ሳይቀር ፈቃዱን እንዲፈጽም ማድረግ የሚችል አምላክ ስላለን የሚያስፈራ የሚችል ምንም ነገር ሊኖር አይገባም፡፡

# ጥናት አስር 1ኛ ቆሮ 6፡1-8

የጥናት ዓላማ፡- ተጎዳሁ ወይም ተበደልኩ ብለን ፍትህ ለማግኘት በአህዛብ ፊት የክርስቶስን ስም ከማስነቀፍ፣ ለወንጌል ሥራም እንቅፋት ከመሆን፤ እኛ ተጎድተንም ወይም ተታለን ለጌታ ነገርን መተው እንደሚሻል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? እናንተ ግን ራሳችሁ ትበድላላችሁ፤ ታታልላላችሁም፤ ያውም እኮ ወንድሞቻችሁን፡፡›› 1ቆሮ 6፡7-8

1. 1ኛ ቆሮ 6፡1-8 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1 ሲነበብ ‹‹በመካከላችሁ›› ሲል ስለ ማን ነው የሚናገረው? በቆሮንቶስ ሰዎች መሃል የተፈጠረው ችግር ምንድነው? ጳውሎስን ይበልጥ ያሳሰበው ችግሩ መኖሩ ነው ወይስ ሰዎቹ ለችግሩ የወሰዱት መፍትሄ ነው? አብራራ
2. በቁ2 መሰረት ሐዋርያው ቅዱሳን በመሃላቸው ለሚፈጠረው ሙግት ለመፍረድ የሚበቁ መሆነቸውን ለማረጋገጥ የተጠቀመበት ሃሳብ ምንድነው? ‹‹ትንሹ ነገር›› ሲል ከምን ጋራ በማነጻጸር ነው?
3. በቁ1-3 ባለው ክፍል ውስጥ የቆሮንቶስ ቅዱሳን እንዲያውቁ የሚጠብቅባቸው ሁለት ነገሮች ፍርድን አስመልክቶ ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ነገሮች መረዳት ለቅዱሳኑ ጠቃሚ የሚሆነው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
4. በቁ5 ላይ ጳውሎስ ፍርድ ቤት ከመሄድ ይልቅ አማራጭ አድርጎ የሚያቀርበው ነገር ምንድነው? በሐዋርያው አመለካከት ያልተስማሙ ሰዎችን እንዲስማሙ ለማድረግ ምን ይጠይቃል?
5. የዛሬውን ምንባብ ስታይ ጸሐፊው ፍርድ ቤትን ይቃወማል በሚለው ሃሳብ ትስማማለህ ወይ? ለምን? ታዲያ ይህ ካልሆነ የዚህ ክፍል ዋና ዓላማው ምንድነው?
6. አማኞች ወደ ፍርድ ቤት ለክስ ሲሄዱ ገና ፍርዱ ሳይሰማ ሁለታችሁም ተሸናፊዎች ናችሁ የሚለው ምን ማለቱ ነው? ሁለቱም ተሸናፊዎች ከሆኑ አሸናፊው ማን ሊሆን ነው? ቁ7ትን ተመልከት፡፡
7. በቁ7-8 ውስጥ የጳውሎስ አጭር ምክር ምንድነው? ይህ ምክር በማቴ 5፡39-42 ኢየሱስ ከተናገረው ንግግር ጋራ ተመሳሳይነቱ ምን ላይ እንደሆነ ተናገር፡፡
8. መብትን መተው አስመልክቶ ለእኛ ዋነኛ ምሳሌ የሚሆነን ማነው? አንተስ የክርስቶስ ስም ከሚነቀፍ፣ ለወንጌል እንቅፋትም ከምሆን እኔ ልጎዳ የሚለው አመለካከት ምን ያህል ውስጥህ ገብቷል? በፊታችን ባለው ሳምንት ዛሬ የተማርከውን እውነት መለማመጃ መድረክ አድርገህ ተጠቀምበት፡፡

# ጥናት አስራ አንድ 1ኛ ቆሮ 6፡9-20

የጥናት ዓላማ፡- ሆሞ ሴክሹዋል ወይም ሴዝቢያን ወይም ደግሞ በማንኛውንም ዓይነት የርኩሰት ህይወት የሚለማመድ ሰው፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በመንፈስ ቅዱስ በመታጠብ፣ በመቀደስና፣ በመጽደቅ አዲስ ህይወት መጀመር የማይችል ምንም ዓይነት ሰው ሊኖር እንደማይችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን…ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል፡፡›› 1ኛ ቆሮ 6፡9-11

1. 1ኛ ቆሮ 6፡9-20 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ9 መሰረት ክርስትያኖች እንዲያውቁት የሚጠበቅባቸው ነገር ምንድነው? ቁ7 እና ቁ9 መታለል የሚኖርብንና የማይኖርብንን ሁለት ዓይነት ሃሳቦች ይጠቁሙናል፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ አብራራ፡፡
2. ቁ11 ላይ ‹‹ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤›› የሚለው አነጋገር የምንን ጊዜ የሚያመለክተን ነው? እነዚህ ሰዎች አሁን ስለሚገኙበት ሁኔታስ ቁጥሩ ምን ይነግረናል? በአንተስ ህይወት ይህ ልዩነት ምን ያህል ጎልቶና ግልጽ ሆኖ ይታያል?
3. በዘመናችን ሰዶማውያን እግዚአብሄር በዚህ ዓይነት እንደፈጠራቸውና በዚሁ መግፋት እንዳለባቸው ይከራከራሉ፡፡ ቁ9ን ስታነብ ስለ እግዚአብሄር አመለካከት ምን ትረዳለህ? ቁ11ድስ ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ምን ተስፋ ሲሰጥ እናያለን?
4. ከቁ 12 ላይ ለክርስትና ህይወት መመሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ጥያቄዎችን በራስህ አማርኛ ጠይቅ፡፡
5. ምግብንና ሆድን አስመልክቶ ጳውሎስ በቁ13 ላይ ያሰፈረው እውነት ምንድነው? ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች እንድንማር የፈለገው እውነት ምን ይመስልሃል?
6. ከቁ9-20 ባለው ክፍል ውስጥ የቆሮንቶስን አማኞች ደጋግሞ የሚጠይቃቸው አንድ ጥያቄ ምንድነው? ጥያቄው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ ተጠይቋል? ከነዚህ ጥያቄዎች መሃል ስንቶቹ በሰውነታችን ላይ ያተኮሩ ናቸው?
7. በቁ15-18 ስንመለከት በትምህርቱ መሃል በማስገባት እንደ ችግር መፍትሄ አድርጎ ያቀረበላቸው ሃሳብ ምንድነው? በቁ19-20 መሰረት በሰውነታችን እግዚአብሄርን ማክበር የሚገባን ምክንያት ለምንድነው? ከ1ኛ ቆሮ 3፡16 እና 6፡19 ስለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት ምን ትማራለህ?
8. ይህ በቁ19 ላይ ተቀበላችሁት የሚለን መንፈስ በቁ11 ላይ ምን ዓይነት ሥራ ሲሰራ ነው የምናየው? ይህንን ዓይነት ሥራ ከሰራባቸው ሰዎች መሃል ምን ዓይነቶች እንደሚገኙበት ጥቂቶቹን ዘርዝር፡፡ በየሥራችንና በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገጥሙን ግብረ ሰዶማውያንን መንፈስ ቅዱስ ሊያጥብ፣ ሊቀድስ፣ ሊያጸድቅ እንደሚችል ታምናለህ ወይ? የጌታ ማዳን ለእነዚህ ሰዎች እንዲዘረጋ በዚህ ሳምንት ጸሎታችን ይሁን፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት 1ኛ ቆሮ 7፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- ባልና ሚስት በነገሮች ላይ ከመነጋገርና ከመወያየት አልፈው በተለይም ደግሞ ሁለቱ በአንድነት በመስማማት የጸሎት ጊዜ ሊኖራቸው እንደሚገባ የእግዚአብሄር ቃል የሚጠቁመን መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በጸሎት ለመትጋት ተስማምታችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ እርስ በእርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ፡፡›› 1ኛ ቆሮ 7፡5

1. 1ኛ ቆሮ 7፡1-11 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ፤ ከምዕራፍ 1-6 ካየናቸው ክፍሎች ይህንን ክፍል የሚለየው ምን ሃሳብ ታያለህ?
2. በቁ2 መሰረት ሐዋርያው ወንዶች ሚስት እንዲኖራቸውና ሴቶችም ባል እንዲኖራቸው የተናገረበት ምክንያት ምን ነበረ? ይህ ቁጥር አንዳንዶች ትክክል እንደሆኑ የሚናገሯቸውን ሁለት አመለካከቶች ልክ እንዳልሆኑ ያረጋግጣል፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን እንደሆኑ አስረዳ፡፡
3. በአውደ ምንባቡ መሰረት ቁ3-4 ላይ ‹‹የሚገባትን›› ‹‹የሚገባውን›› የሚሉት አባባሎች የሚናገሩት ስለምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች መሰረት ሰውነታችን የማን ነው? ሰውነቱ የራሱ ብቻ እንዲሆን የሚፈልግ ሰው ያለው አማራጭ ምንድነው ትላለህ?
4. በቁ5-6 ትን በማንበብ ባለትባለትዳሮች ለሰይጣን እድል ፈንታ ሊሰጡት ይችላሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? አዎን ይህንን ለማለት ያስቻለህ ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ባለትዳሮች ይህንን ሁኔታ ማስቀረት እንዲችሉ የተመከሩት ምክር ምንድነው?
5. ጳውሎስ በቁ7-8 ላይ ለሰው ሁሉ የሚመኘው ነገር ምንድነው? ይህንን ማለቱስ ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በጳውሎስ ምኞትና በተጨባጩ ሁኔታ መሃል ስላለው ልዩነትስ ምን ይታይሃል? ለዚህስ የሚሰጠን ምክንያት ምንድነው?
6. ማቴ 5፡32 ትንና ማር 10፡9 በማንበብ ጸሐፊው በቁ10-11 ላይ ‹‹…ይህም ትዕዛዝ የጌታ እንጂ የእኔ አይደለም፡፡›› ማለቱ ምን ለማለት ፈልጎ ነው ትላለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለባልና ለሚስት የተሰጠው አንድ ትዕዛዝ በአንድ ቃል ጠቅልል ብትባል ምን ትላለህ? በማናቸውም ምክንያት የመለያየት ሁኔታ ከተፈጠረ የተሰጣቸው ሁለት አማራጮች ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
7. ወደ ቁ5 ተመልሰን ስንመለከት ‹‹ተስማምታችሁ›› ማለቱ ለመስማማት በቅድሚያ በሁለቱ መሃል መካሄድ ያለበት ነገር ምንድነው ትላለህ? በዚሁ ቁጥር ላይ በጳውሎስ አመለካከት ባልና ሚስት በአንድነት ሊያደርጉ የሚጠበቁባቸው ሁለት ቁልፍ ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
8. ያለእነዚህ ሁለት ነገሮች ትዳርን ለማቆም እጅግ አዳጋች ይሆናል በሚለው ሃሳብ ትስማማለህ ወይ? ለምን? ያገባህ ከሆነ እነዚህን ምክሮች በሥራ ለመተርጎም በጌታ ሃይል ቁርጥ ውሳኔ አድርግ፡፡ ያላገባህ ከሆነ ደግሞ መልካም ጅማሬ እንዲሆንልህ ጌታ ያስተማረህን በልብህ ይዘህ አቆየው፡፡

# <u>ጥናት አስራ ሶስት 1ኛ ቆሮ 7፡12-24</u>

የጥናት ዓላማ፡- አማኝ የሆነ ሰው ሊያተኩር የሚገባው ከጌታ ባራ ባለው የግንኙነት ቅርበት ላይ እንጂ፤ በሚሰራው የሥራ ዓይነት፣ በትምህርት ደረጃው፣ በሃብቱ መጠንና በመሳሰሉት ራሱን መለካት እንደማይኖርበት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹መገረዝም ሆነ አለመገረዝ አይጠቅምም፤ ዋናው ነገር የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ መፈጸሙ ነው፡፡…ወንድሞች ሆይ እያንዳንዱ ሰው በተጠራበት ሁኔታ ከእግዚአብሄር ጋራ ጸንቶ ይኑር፡፡›› 1ኛ ቆሮ 7፡19፣ 24

1. 1ኛ ቆሮ 7፡12-24 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ12 ላይ ‹‹ለሌሎቹ›› ከሚላቸው ሌላ በምዕ 7 ላይ ትዳርን አስመልክቶ ስለስንት ዓይነት ሰዎች ትዕዛዝ ሰጥቷል? ዘርዝራቸው፡፡ ‹‹ይህንን የምለው እኔ እንጂ ጌታ አይደለም›› ለሚለው አነጋገር ያለህን መረዳት ተናገር፡፡
2. በቁ12-13 መሰረት ከማመናችን በፊት ስለገባንበት ትዳር ምን ያዘናል? በቁ15-16 መሰረት ከዚህ ዓይነቱ ትዳር ለመውጣት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ጳውሎስ የሰጠው አንድ ነገር ምንድነው?
3. 1ኛ ቆሮ 7፡15፣ ሮሜ 7፡2፣ ማቴ 19፡8-9 እነዚህን ሶስት ክፍሎች በማንበብ ፍቺን አስመልክቶ ምን ነገሮችን መረዳት ይቻላል ትላለህ? ቁ16 ላይ የጠየቀው ጥያቄ ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
4. ቁ17 ላይ የጳውሎስ መመሪያ ወይም ምክር ምነድነው? በዚህ ክፍል የተሰጠው ምክር ወይም መመሪያ የሚሰራው ለማን ነው ይላል ጳውሎስ?
5. ቁ18-20 ስናነብ በቁ17 ላይ የሰጠውን መመሪያ ተግባራዊነት ከሃይማኖት ጋራ በተያያዘ መልኩ ለማስረዳት የተጠቀመበት ምንድነው? በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ሃሳብ ከአህዛብ ይልቅ ለአይሁዶች ሊያስቸግር የሚችለው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ19 መሰረት እነዚህ ሰዎች ልባቸውን ከመገረዝና ካለመገረዝ አንስተው ወደየት እንዲያደርጉ ነው የሚያሳስባቸው? በቁ20 ላይ ከሰጠው ትዕዛዝ አንጻር የተገረዙትን ምንድነው የሚላቸው? ያልተገረዙትንስ?
7. ቁ21 ላይ ጸሃፊው በዘመኑ ህብረተሰቡን የሚከፍል የነበረ በማስረጃነት የጠቀሰው ነገር ምንድነው? ምክሩ በቁ21 ላይ በተለይም ለባሪያዎች ምን ነበረ? ‹‹ነጻነትህን ማግኘት ከቻልክ ግን ነጻነትህን ተቀበል›› የሚለው አነጋገር ምን እውነት ይጠቁመናል?
8. ለምንድነው ባሪያው መጨነቅ የማይኖርበትና፣ ጌታው ደግሞ ሊኩራራና ሊታበይ የማይገባው? ከዚህ ክፍል አንጻር ውጫዊ ሁኔታዎቻችን?
9. በዘመናችን አለመገረዝና ባርነት ጭንቀቶቻችን አይደሉም፡፡ ሰዎችን በዛሬ ዘመን ጭንቀት ሊሆኑባቸው የሚችሉ ምን ውጫዊ ነገሮች መጥቀስ እንችላለን? ከጌታ ጋራ ሊኖረን ከሚገባው ግንኙነት ጋራ ሊኖራቸው ስለሚገባው ቦታ ምን ትረዳለህ? ዋናው ነገር ለጌታ የመታዘዝ ህይወትና ከእርሱ ጋራ የቅርብ ግንኙነት ማዳበር እንጂ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራህ ዓይነት፣ ወይም ማናቸውም ዓይነት በህብረተሰቡ መሃል ያለህ ሥፍራ ስላልሆነ ትኩረትህን በዋነኛው ነገር ላይ አድርገው፡፡

# ጥናት አስራ አራት 1ኛ ቆሮ 7፡25-40

የጥናት ዓላማ፡- ከማናቸውም በትዳር ውስጥ ከተጠመዱ ባልና ሚስቶች ከሚጠበቁባቸው የተለያዩ ሃላፊነቶች መሃል፤ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ደግሞ ባሏን ደስ ሊያሰኙ የሚችሉበትን መንገድ ሁሉ ማሰብ እንደሚጠበቅባቸው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ያገባ ሰው ግን ሚስቱን ደስ ለማሰኘት የዚህን ዓለም ነገር ያስባል…ያገባች ሴት ግን ባሏን ደስ ለማሰኘት የዚህን ዓለም ነገር ታስባለች፡፡›› 1ኛ ቆሮ 7፡33-34

1. 1ኛ ቆሮ 7፡25-40 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ25-26 ውስጥ የጳውሎስ ምክር ለደናግሉ ምንድነው? ይህ አይነቱ ምክር ስላስፈለገበት ምክንያት ጸሃፊው ምን ይነግረናል?
2. በቁ28 ላይ ጳውሎስ የሚናገረው ችግር ምን ዓይነት ችግር ይመስልሃል? ይህንን ዓይነት አነጋገሩን ስትመለከት ሰዎችን ወደ ትዳር እንዳይገቡ የሚያስፈራራ ይመስልሃል ወይስ ቆም ብለው ሳያስቡበት ወደ ትዳር እንዳይገቡ የሚያስጠነቅቅ ይመስልሃል? አስረዳ፡፡
3. በቁ29-31 ላይ ‹‹ሚስት ያላቸው እንደሌላቸው ሆነው ይኑሩ፡፡ የሚያለቅሱ እንደማያለቅሱ…›› ስላለበት የሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? ትዳርን፣ ሃዘን፣ ደስታንና የመሳሰሉት በማንሳት ሊያሳያቸው የሚመክረው ዋነኛ ሃሳብ ምን ይመስልሃል?
4. ቁ32-35 ባለው ክፍል መሰረት ባገባ ሰውና ባላገባ ሰው መሃል ስላለው ልዩነት ምን ይነግረናል? ጳውሎስ ይህንን ሲናገር ዓላማው ምን ነበረ?
5. በቁ39 ላይ ከትዳር አንጻር ማየት የምንችላቸው ቢያንስ አራት ሃሳቦችን ተናገር፡፡ ከነዚህ ከዘረዘርካቸው አራት ሃሳቦች መሃል ቀድሞ በዚህ መልኩ ተመልክቼው አላውቅም የምትለው ሃሳብ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡
6. ቁ40 ላይ ይህች ባሏ የሞተባት ሴት ሳታገባ መኖሯን የመረጠላት ለምንድነው? በዚህ መልስህ መሰረት ለማግባትና ላለማግባት መጠየቅ ከሚኖሩብን ብዙ ነገሮች መሃል ዋነኛው ምን መሆን አለበት ማለት ነው?
7. ትዳርን አስመልክቶ በአጠቃላይ ከ1ኛ ቆሮ 7 ለሰዎች ምርጫ የተተው ምን ነገሮችን ትመለከታለህ? ለሰዎች ምርጫ ያልተተውትስ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. ወደ ቁ32-35 መለስ ብለን ስናይ ስላገባ ሰው ሲናገር ‹‹ያስባል›› ወይም ‹‹ታስባለች›› ተብሎ በተደጋጋሚ ተነግሯል፡፡ እነዚህ ሰዎች ያስባሉ በተባለው ነገር ውስጥ የሚጠቃለሉት ምን ዓይነት ሃሳቦች ናቸው? ከዚህ ልንማር የምንችለው እውነት ምንድነው? ሚስትህን ወይም ባልሽን ደስ ለማሰኘት ምን ያህል ታስባለህ/ሽ?

# ጥናት አስራ አምስት 1ኛ ቆሮ 8፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- በክርስቶስ ያገኘነውን ነጻነት በትክክል መጠቀም ካልቻልን መልሰን የእርሱን ቁስል የምንወጋበት መሳሪያ ልናደርገው እንደምንችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በዚህ መንገድ ወንድሞቻችሁን በመበደልና ደካማ ህሊናቸውን በማቁሰል፤ ክርስቶስን ትበድላላችሁ…ወንድሜን ላለማሰናከል ስል ከቶ ሥጋ አልበላም፡፡›› 1ኛ ቆሮ 8፡12-13

1. 1ኛ ቆሮ 8፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ውስጥ በተለያየ መልኩ በብዛት የተጠቀሰ ሃሳብ ምንድነው? ይህ ሃሳብ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል?
2. በቁ1-3 ላይ እውቀትን ካለማወቅ ጋራ ሳይሆን ከምን ጋራ ያወዳድረዋል? በነዚህ ቁጥሮች አማካኝነት ሊያስተላልፍ የፈለገው እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ይህን ሲል እውቀት አስፈላጊ አይደለም ማለቱ ነው ወይ? አስረዳ፡፡
3. በቁ4-6 መሰረት ጣዖትንና እግዚአብሄርን አስመልክቶ አማኝ ሊኖረው ስለሚገባው አመለካከት የተናገረውን ሃሳብ በአጭር ዓረፍተ ነገር በመጠቅለል ተናገር፡፡ በቁ5 ላይ ባሉት አማልክትና በእግዚአብሄር መሃል ስላለው ልዩነት ይህ ክፍል የሚናገራቸው ሃሳቦች ምን ምንድናቸው?
4. ቁ7 ‹‹ይህን የሚያውቁ ሁሉም አይደሉም›› በዚህ አነጋገር ይህ በመባል የተጠቀሰው ነገር ምንድነው? ሁሉም በተባለው ሃሳብስ የሚጠቃለሉት እነማን ናቸው?
5. ቁ7-8 ላይ በተለይ ቁ7 የሚናገረው ስለምን ዓይነት ሥጋ ነው? ይህ ዓይነቱን ሥጋ መብላት ለምንድነው ለአንዳንዶቹ መሰናከል የሚሆነው? ቁ8 ምግብ በመንፈሳዊ ህይወታችን ላይ ስላለው አስተዋጽዖ ምን ይናገራል?
6. በቁ9 ላይ ነጻነት እንዳላቸው ሆነው የሚነገርላቸው እነማን ናቸው? በዮሐ 8፡32 ካለው ሃሳብ ጋራ ይህንን ክፍል በማነጻጸር ተናገር፡፡ በዚሁ ቁጥር ላይ ደካሞች በመባል የተጠቀሱትስ የትኞቹ ሰዎች ናቸው? ከድካማቸው ለመላቀቅ ምን ያስፈልጋቸዋል ትላለህ?
7. ቁ9-11 ነጻነቱን በተረዳውና በደካማው አማኝ መሃል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ምን ያስተምረናል? ቁ11 ላይ ‹‹…በአንተ እውቀት ምክንያት ጠፋ ማለት ነው›› የሚለው አነጋገር ለቁ1 ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
8. በቁ12-13 አነጋገር ነጻነታችንን ያለአግባብ በመጠቀማችን ምክንያት የምንጎዳው ማንን ነው? ከዚህ በመነሳት ጳውሎስ የደረሰበት ውሳኔ ምንድነው? ለወንድምህና ለክርስቶስ ስትል የምትወደውን ዋነኛ ነገር ለመጣል ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ? ለዚህ ብለህ የጣልከው ነገር በህይወትህ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት 1ኛ ቆሮ 9፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- የወንጌል አገልጋይ ነን የሚሉ ሁሉ በሰዎች ህይወት ውስጥ የሚዘሩት መንፈሳዊ ዘር መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸውና፤ በአገልግሎታቸው የሚጠቀሙት ሰዎች ደግሞ ለሥጋቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር መሟላት መንፈሳዊ ግዴታቸው መሆኑን መገንዘብ እንደሚኖርባቸው ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኛ በእናንተ መካከል መንፈሳዊ ዘር ዘርተን ከሆነ ለሥጋ የሚሆን ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆኑ ነውን?›› 1ኛ ቆሮ 9፡11

1. 1ኛ ቆሮ 9፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ የተጠየቁት ጥያቄዎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ጠያቂው የጥያቄዎቹን መልስ ስለማያውቅ ነው ወይስ ለምን የጠየቀ ይመስልሃል? አስረዳ፡፡
2. በቁ4-5 የተጠየቁት ጥያቄዎችስ ምን ምንድናቸው? በቁ1-2 ባሉትና በቁ4-5 ባሉት ጥያቄዎች መሃል የምታያቸው ልዩነቶች ምንድናቸው? ተመሳሳይነታቸውስ?
3. ቁ7 ላይ የተጠየቁት ሶስቱ ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው? በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ወታደርን፣ ገበሬንና እረኛን ሲያመጣ ሊያስተላልፍ የፈለገው ነገር ምንድነው?
4. በቁ7 ላይ የሰነዘራቸው ጥያቄዎችና (በሰው አመለካከት ላይ ተመስርቶ)፤ በቁ8-10 (በእግዚአብሄር ቃል ላይ ተመስርቶ) የሚናገረው ሃሳብ እንዴት ነው ሊደጋገፉ የሚችሉት? ምንም እንኳን ቁ7 ሙሉ ለሙሉ ስሜት የሚሰጥ ሃሳብ ሆኖ ሳለ፤ በእግዚአብሄር ቃል መደገፉ ምን ያስተምረናል?
5. ቁ11-12ትን ስናነብ ከሥጋዊና ከመንፈሳዊ ነገር የትኛው እንደሚበልጥ ነው የሚጠቁመን? በምን ምክንያት ነው ጳውሎስ ከሌሎቹ ይልቅ ክፍያ ሊጠይቁ መብት እንደሚኖረው የተናገረው? መብቱን ስለተወበትስ ምክንያት ምንድነው ከነዚህ ቁጥሮች የምናነበው?
6. በቁ13 ላይ በወንጌል አገልግሎት የተሰማሩ ሰዎች ያላቸውን መብት ለማስረዳት የተጠቀመባቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎችና በቁ9-10 ያሉት ክፍሎች የትኛውን ኪዳን ይወክላሉ ትላለህ?
7. ቁ14 ላይ ሐዋርያው ይህንን የአገልጋዮች መብት ለመደገፍ የሚጠቀምበት ሌላ ሃሳብ ምንድነው? ይህንን አስመልክቶ ጌታ የተናገረውና ወደ አዕምሮህ የሚመጣ ጥቅስ ካለ ተናገር፡፡
8. ከቁ1-15 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የወንጌል አገልጋይ ከወንጌል ቀለቡን ማግኘት እንዳለበት ለማረጋገጥ የተሰነዘሩትን ቢያንስ ሶስት ሃሳቦች የት ቁጥር ላይ እንደሚገኙ ጠቁም፡፡ በቁ11 መሰረት አገልጋዮች ራሳቸውን መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄ ምን ይመስልሃል? ተገልጋዮቹስ? በህይወትህ ኑሯቸውን በሰዎች ህይወት መንፈሳዊ ነገርን ብቻ በመዝራት የተሰለፉ ሰዎችን ግዴታህ እንደሆነ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት አስራ ሰባት 1ኛ ቆሮ 9፡16-27

የጥናት ዓላማ፡- በማናቸውም አገልግሎት መስክ የተሰማራን ሁላችን፤ አሸንፎ ሽልማት ለመቀበል እንደሚሮጥ ስፖርተኛ ራስን በመግዛት እንድንሮጥ እንጂ ሩጫን ለመጨረስ ያህል ብቻ እንደተሰለፈ ተወዳዳሪ የግብር ይውጣ ዓይነት አገልግሎት የምናገለግል መሆን እንደሌለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ስለዚህ ሽልማቱን እንደሚቀበል ሰው ሩጡ፡፡›› 1ኛ ቆሮ 9፡24

1. 1ኛ ቆሮ 9፡16-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ16-18 ላይ ያለው ክፍል ያተኮረበት ዋነኛ ነገር ምንድነው ትላለህ? ‹‹ወንጌልን መስበኬ አያስመካኝም፤ የምሰብከው ግዴታዬ ስለሆነ ነው›› የሚለው አነጋገር እንዴት እንደምትረዳው ግለጽ፡፡
2. ቁ17-18 መሰረት ሐዋርያው የወንጌል ግዴታውን ሊወጣ የሚችልባቸው ሁለቱ የተለያዩ መንገዶች ምንና ምንድናቸው? ሽልማት የሚያስገኘው የትኛው መንገድ ነው? ሽልማቱስ ምንድነው?
3. በቁ19 ላይ ጳውሎስ ስለማንነቱ የሚነግራቸው ነገር ምን እንደሆነ ነው? ለማንም ባሪያ ያልሆነው ጳውሎስ ለምንድነው ራሱን ለሰው ሁሉ ባሪያ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነው? አንተስ ለወንጌል ስትል ምን ያህል ለሰዎች ባሪያ ለመሆን ፈቃደኛ ነህ?
4. ቁ20-23ትን ስናይ ጳውሎስ ሊደርሳቸው የጠቀሳቸው ስንት ዓይነት ቡድኖች ታያለህ? እነማን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ የጳውሎስ ጥረት እዚህ ከተጠቀሱት አራት ቡድኖች ያለፈ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁመን የትኛው ጥቅስ ነው?
5. ከላይ በተመለከትናቸው ቁ20-23 ባሉት ክፍሎች ውስጥ በብዛት የሰፈረ አንድ ሃሳብ ምንድነው? ይህ ሃሳብ በእነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? ስለዚህ ጳውሎስ በዚህ ክፈል መሰረት ይህንን ለማድረግ የተነሳሳባቸው ምክንያቶች ሁለት ናቸው ብንል ምንና ምንድናቸው ትላለህ?
6. ጳውሎስ የሚያደርገው ይህ ጥረት በሰዎች ሁሉ ህይወት ላይ ፍሬ ያፈራል ማለት እንዳልሆነ የሚያመለክተን የትኛው ሃሳብ ነው? የዚህን መልስ ስንመለከት ለእኛ ማበተታቻ የሚሆነን በምን መንገድ ይመስልሃል?
7. ቁ24-27 ላይ ከምታነበው ምሳሌ በመነሳት፤ የሯጮችን ብዛትና ሽልማት አቀባበልን አስመልክቶ ምድራዊና ሰማያዊ ሯጮችን በማወዳደር ተናገር፡፡ በተለይ በቁ25 መሰረት ሽልማት ለማግኘት ከሚሮጥ ሰዎ የሚያልፍባቸው ሁለት ዓይነት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
8. ጳውሎስ በቁ26-27 ላይ አገልግሎቱን አስመልክቶ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው? ቁ24 ላይ አንባቢዎቹን ሁሉ የሚመክረው አንዱ ምክር ምንድነው? ሽልማት እንደሚቀበል ሰው መሮጥ ሲባል የሚገባህ ነገር ምንድነው? ሩጫህን ስትሮጥ ወይም አገልግሎትህን ስታገለግል ምን ያህል ለሽልማት እንደምትበቃ ሆነህ ታገለግላለህ? ከጌታ ዘንድ ዋንጫህን ለመቀበል ራስህን በመግዛትና፣ የሚያደክም እንኳን ቢሆን ግብ እንዳለው ሰው ሆነህ በትጋት አገልግል፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት 1ኛ ቆሮ 10፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- በረከቶቹን ከመቀበልም አልፎ የእግዚአብሄርን ህዝብ የመራው ሙሴ እንኳን የተስፋይቱን አገር እንዳልገባባት ስንመለከት፤ እኛም ምን ያህል በጥንቃቄ፣ በትህትናና ራስን በመግዛት ህይወታችንን መምራት እንደሚገባን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ተደላድዬ ቆሜአለሁ የሚል ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፡፡ በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሄር ታማኝ ነው…›› 1ኛ ቆሮ 10፡12-13

1. 1ኛ ቆሮ 10፡1-13 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-4 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ‹‹አባቶቻችን›› እያለ የሚናገርላቸው እነማን ናቸው? እነዚህ አባቶች የተለማመዷቸውን ቢያንስ አራት ነገሮች ተናገር፡፡
2. ስለ እነዚህ አባቶች ያነበብነውን ልምምዶች በእኛ ህይወት ከተለማመድነው ጋራ በማነጻጸር ተናገር፡፡ ከዚህ ክፍል ስለጠጡት መጠጥ ምን ለየት ያለ ነገር ትመለከታለህ? አስረዳ፡፡
3. ስለ እነዚህ ሰዎች መጨረሻ ቁ5 የሚነግረን ምንድነው? በክፍሉ መሰረት ስንቶቹ ናቸው በምድረበዳ የቀሩት? ስለዚህ ታሪክ ያለህን መረዳት በመጠቀም ብዙዎች የሚለውን ቁጥር ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡
4. ቁ6-10 ባለው ክፍል እነዚህ አባቶች የፈጸሟቸው አምስት ሃጥያቶች ምን ምንድናቸው? በእያንዳንዶቹ የሃጥያት ዓይነቶች ስለተፈተኑትና ስለወደቁት ሰዎች ቁጥር ምን ይነግረናል? የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ፈተናዎች መውደቃቸው ምን ያስተምርሃል?
5. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የትኞቹ ሃጥያቶች ናቸው ከነቅጣታቸው የሰፈሩት? የእግዚአብሄርን በረከትና ጥበቃ የተለማመዱ ሰዎች የዚህ ዓይነት ቅጣት መቀበላቸው ምን የሚያስተምረን ነገር ያለ ይመስልሃል?
6. የእነዚህን ሰዎች የተዘረዘሩ ሃጥያቶች ስትመለከት በእኛ ዘመን ለብዙዎች ውድቀት ሆኖ የምታየው የትኛውን ሃጥያት ነው? በቁ11 መሰረት ይህንን ሁሉ ነገር መንፈስ ቅዱስ በጽሑፍ ያሰፈረው ለምንድነው ይላል?
7. ቁ11-12 ስታነብ ‹‹እኛ›› በማለት የሚያጠቃልለው እነማንን ነው? ይህ ክፍል ‹‹እኛ›› ከሚላቸው ሰዎች በማጥበብ ትኩረቱን በማን ላይ ሲያደርግ ታያለህ? አዲሱም ሆነ የቆየው ማስጠንቀቂያ መግኘቱ ለእያንዳንዳችን ምን ትምህርት ይሰጠናል?
8. ዛሬ ካጠናነው ክፍል በመነሳት መጠንቀቅ የሚኖርብንን ቢያንስ አራት ዓይነት ነገሮች ዘርዝር፡፡ ቁ13 የእግዚአብሄርን ታማኝነት ማወቅህ የምታልፍበትን ፈተና ለመወጣት እንዴት ያበረታታሃል? እግዚአብሄር ያሰበልህን ለመውረስ ምን ያህል በጥንቃቄና ሥጋህን በመግራት ትኖራለህ? ልብህን በመንገድህ ላይ አድርገህ በጥንቃቄ ተራመድ፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 10፡14-11፡1

የጥናት ዓላማ፡- እያንዳንዱን ሰው እንደማንነቱ መቀበልና፤ ማናቸውንም የወንጌል እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ማስወገድ ብዙዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ መንገድ ሊጠርግ የሚችል ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በሚቻለኝ ሁሉ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፣ ከሁሉም ጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ፡፡ ይህንን ሁሉ የማደርገው፣ ከወንጌል በረከት እካፈል ዘንድ፣ ስለ ወንጌል ብዬ ነው፡፡›› 1ኛ ቆሮ 9፡22-23፣ 1ኛ ቆሮ 10፡32-33

1. 1ኛ ቆሮ 10፡14-11፡1 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ14 ላይ አንባቢዎቹን የሚያዛቸው ትዕዛዝ ምንድነው? ይህንን ክፍል ጨምሮ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አማኞች እንዲሸሹ የተነገራቸው ቢያንስ አራት ነገሮችን ተናገር፡፡ 1ኛ ቆሮ 6፡18፣ 1ኛ ጢሞ 2፡22፣ 2ኛ ጢሞ 6፡11ድን ማንበብ ይረዳል፡፡
2. በቁ14-22 በየት ስፍራ ስለሚበላው ምግብ ነው ትኩረት አድርጎ የሚናገረው? በነዚህ ቁጥሮች ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች በአንድ አረፍተ ነገር ማጠቃለል ቢያስፈልግ ምን ትለዋለህ?
3. በቁ23 ላይ የሚጠቅሳቸውን ሁለት ሃሳቦች በራስህ ቃላት ምን ማለቱ እንደሆነ የሚገባህን ለወገኖች ተናገር፡፡ ቁ24 እነዚህን እውነቶች በተጨማሪ ማየት ስለሚገባን ነገር ምን ይጠቁመናል?
4. ቁ25-26ትስ በየት ስፍራ ላይ ስለሚበላ ምግብ ነው ትኩረቱ? ከዚህ አንጻር የሃዋርያው ምክር ምንድነው?
5. ቁ27-30 ደግሞ የትኛውን ሥፍራ አስመልክቶ ነው ምክር የሚሰጠው? ምክሩ በገበያ ሥፍራ ከሰጠው ምክር ጋራ እንዴት ይመሳሰላል? እነዚህንስ ሁለት ሁኔታዎች የሚለያቸው ከምክሩ አኳያ ምንድነው?
6. እያንዳንዱን ሊገጥመን የሚችለውን ሁኔታ ሁሉ መዘርዘር ስለማይቻል ሃዋርያው በዛሬው ምንባብ ውስጥ የተወልን ዋነኛ መመሪያ ምንድነው ትላለህ? ይህንን መመሪያ መለማመድ ሊያስገኝ የሚችላቸውን መንፈሳዊ ጥቅሞች ተወያዩባቸው፡፡
7. በቁ33 ላይ ጳውሎስ ሰውን ሁሉ ለማስደሰት እጥራለሁ ሲል የሚሰብከውን ወንጌል ሰዎችን ሁሉ ደስ በሚል መንገድ አቀርበዋለሁ ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ እንደሆነ ሃሳብህን በእግዚአብሄር ቃል በመደገፍ አስረዳ፡፡ ጳውሎስ ለማስደሰት የሞከራቸው ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ብሎ ያምናል ወይ? አስረዳ፡፡
8. በ1ኛ ቆሮ 9፡22-23 የሚገኘው ጥቅስ፤ በ1ኛ ቆሮ 11፡32-33 ላለው ሃሳብ ምን ተጨማሪ መረጃ ይሰጠናል? ብዙዎች እንዲድኑ በአንተ በኩል የምታደርገው ጥረት ምንድነው? እያንዳንዱን ሰው የምትቀርብበት ሁኔታ ብዙዎችን ወደ ደህንነት ወይም በተቃራኒው ለብዙዎች እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ተመላለስ፡፡

# <u>ጥናት ሃያ 1ኛ ቆሮ 11፡2-16</u>

የጥናት ዓላማ፡- በቃሉ ውስጥ በጊዜው ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት የሚያስቸግሩን እውነቶች እንደሚኖሩ መገንዘብና፤ እግዚአብሄር ደግሞ ከእኛ ጋራ በመደራደር የሚቀይረው ነገር አለመኖሩን ተረድተን በትህትና ተቀብለን መታዘዝ መለማመድ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ ማንም በዚህ ጉዳይ ላይ መከራከር ቢፈልግ፣ እኛም ሆን የእግዚአብሄር አብያተ ክርስትያናት ከዚህ የተለየ ልማድ የለንም፡፡›› 1ኛ ቆሮ 11፡16

1. 1ኛ ቆሮ 11፡2-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ2 ላይ ሐዋርያው የቆሮንቶስ ሰዎችን የሚያመሰግንባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? 1 ቆሮ 11፡17 ትና 11፡22 ላይ ደግሞ በተቃራኒው አላመሰግናችሁም በማለት ይናገራቸዋል፡፡ ከዚህ አሰራሩ ምን ትምህርት መቅሰም እንችላለን?
2. በቁ3 ላይ ጸሐፊው አንባቢዎቹ ማወቅ አለባችሁ የሚላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ከእነዚህ ሶስት እውነቶች መሃል ሰዎች ብዙ ጊዜ ለመቀበል ትግል የሚሆንብን እውነት የትኛው ነው? ለምን ይመስልሃል ይህ የሚሆነው?
3. ቁ4-5ትን ስታነብ ወንድ ራሱን (ክርስቶስን) የሚያዋርደው ምን ሲያደርግ ነው? ሴትስ ራሷን (ወንድን) የምታዋርደው ምን ስታደርግ ነው?
4. ቁ6-7 ባሉት ቁጥሮች በመመልከት ወንድ ራሱን መከናነብ የማይኖርበት ምክንያት ለምንድነው ይላል? ሴት ከወንድ ጋራ ስላላት ግንኙነትስ ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?
5. ቁ8-10ን ስታይ ወንድ ከሴት ሳይሆን ሴት ከወንድ ተገኘ፤ ወንድ ለሴት ሳይሆን ሴት ለወንድ ተፈጠረች፤ የሚሉት ሃሳቦች የመጡበትን ክፍል ተናገር፡፡ እነዚህን ሃሳቦች ያመጣው የትኛውን እውነት ለመደገፍ ነው?
6. ቀደም ብሎ የተናገረውን ሃሳብ ምናልባትም ወንዶች በተሳሳተ መንገድ እንዳይወስዱት ሚዛን የሚያስጠብቅ ሃሳብ በቁ11-12 ውስጥ ምን ታያለህ? ‹‹በጌታ ዘንድ›› እና ‹‹የሁሉም መገኛ እግዚአብሄር ነው›› የሚሉትን ሃሳቦች ይህንን ምንባብ ለመረዳት የሚጠቅሙት በምን መነገድ ነው ትላለህ?
7. በቁ13-16 ላይ ማንን ነው ፈራጅ አድርጎ የሚያቀርበው? ዋነኛ ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ነገር ምንድነው? በዚህ ቦታ ላይ ከምን አንጻር እንዲፈረድ ነው ጸሐፊው የሚጠይቀው?
8. በዛሬው ምንባብ ውስጥ ጳውሎስ የሰጠው መመሪያ ለቆሮንቶስ ቤ/ክርስትያን ብቻ እንዳልሆነ የሚነግረን የትኛው ክፍል ነው? ይህንን እውነት በትህትና መቀበልና መታዘዝ እንደሚኖርብህ የሚያረጋግጥልህ የትኛው ጥቅስ ነው? ከዘመኑና ከአካባቢው ጋራ የማይስማማ ሲሆን ቃሉን ለመታዘዝ ትጋ፡፡

<u>ጥናት ሃያ አንድ 1ኛ ቆሮ 11፡17-34</u>

የጥናት ዓላማ፡- የጌታን ራት ከመካፈል ሊያግደን የሚገባው ነገር ሃጥያተኛነታችን ሳይሆን፤ ሃጥያት በውስጣችን እንዳለ እያወቅን ራሳችንን ሳንመረምር፤ በግድየለሽነት ሃጥያታችንን ሳንናዘዝ መቅረባችን መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንግዲህ ማንም ሳይገባው፤ ይህን እንጀራ ቢበላ ወይም የጌታን ጽዋ ቢጠጣ፤ የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ ይሆናል፡፡ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ከመብላቱና ከዚህ ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን ይመርምር፤›› 1ቆሮ 11፡27-28

1. 1ኛ ቆሮ 11፡17-34 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ17-18 አነጋገር ጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ስብሰባ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? በስብሰባቸው መሃል ከሚገለጡት ነገሮች መሃል ግልጽና ዋነኛ አድርጎ የተመለከተው ችግር ምንድነው?
2. በቁ19 ላይ ሐዋርያው የተናገረውን አነጋገር እንዴት እንደምትረዳው ለወገኖች አካፍል፡፡ በዚህ ቁጥርና በ1ኛ ቆሮ 10፡5 መሃል ምን የሃሳብ ተመሳሳይነት ይታይሃል?
3. ቁ20-21 ላይ እነዚህ ሰዎች ስለሚካፈሉት የጌታ ራት ጳውሎስ የደመደመው ምን በማለት ነው? እነዚህ ሰዎች ከሚያደርጉት ነገሮች ይህንን ለማለት ያስቻሉት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
4. ቁ22 ላይ የሚጠይቃቸው ሶስት ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው? በቁ21 ላይ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ጳውሎስ በቁ22 ላይ እንደምን አድርጎ ነው ያቀረበው?
5. በቁ23-26 ላይ ስናነብ ስለ ሥጋውንና ደሙን ሊኖረን ስለሚገባን አመለካከት ምን ምን ነገሮችን መማር እንችላለን? በነዚህ ቁጥሮች መሰረት ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? ይህንን አንድ ነገር እያደረግህ ትገኛለህ ወይ?
6. በቁ27-29 መሰረት ሰው የጌታን ሥጋና ደም ለመውሰድ ከመቅረቡ በፊት የሚጠበቅበት አንድ ነገር ምንድነው? ለምንድነው ይህንን ነገር ማድረግ የሚኖርበት?
7. ቁ30-32 ሥጋና ደሙን በማይገባ መንገድ በመውሰዳቸው ምክንያት በሰዎቹ ላይ ደረሰ የሚላቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በእነዚህ ቁጥሮች አነጋገር ለፍርድ ምክንያት ሆኖ የቀረበው ነገር ምንድነው? ጌታ የሚገስጸን ምክንያት ለምንድነው? ከዚህ ድርጊቱ ሰለ ጌታ ምን እንደምትማር ለወገኖች ተናገር፡፡
8. በመጨረሻዎቹ ሁለት ቁጥሮች ማለትም በቁ33 ና 34 የጳውሎስ ምክር ምንድነው? ከዚህ ክፍል በመነሳት ሃጥያተኛ ነኝ፤ ስለዚህም የጌታን ራት መካፈል አልችልም ለሚልህ አማኝ ከዚህ መልካም ነገር መካፈል እንዲችል የምትመክረው ምክር ምንድነው? ደሙና ሥጋው ለአንተ ለሃጥያተኛው የተሰጠ ስለሆነ ራስህን በመመርመር፣ ሃጥያትህን በመናዘዝና በአክብሮት የበረከቱ ተካፋይ እንደምትችል አትጠራጠር፡፡

# ጥናት ሃያ ሁለት 1ኛ ቆሮ 12፡1-11

የጥናት: መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንደፈቀደና እንደመሰለው ሥጦታዎችን እንደሚያድል፤ እኛም አማኞች ደግሞ እርስ በእርስ እንድንገላገልበት ከእርሱ የተቀበልነውን ሥጦታ አክብረን በመያዝ ለጋራ ጥቅም ማዋል እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡›› 1ኛ ቆሮ 12፡7

1. 1ኛ ቆሮ 12፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ ጳውሎስ ከቁ1-3 ባለው ክፍል ላይ አንባቢዎቹ እንዲያውቁ የሚፈልገው ነገር ምንድነው ይላል? በዚህ ክፍል ውስጥ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ዘወር ከማለታቸው በፊት ስለነበራቸው ህይወት ሊያስታውሳቸው የፈለገው ነገር ምን ነበረ?
2. በቁ3 ከሚናገረው አነጋገሩ ላይ ጸሃፊው በእርግጠኛነት የሚነግራቸው ሁለት መንፈሳዊ እውነቶች ምንና ምንድናቸው? ይህንን ሲል ማንም ሰው ይህንን ዓይነት ቋንቋ ከአንደበቱ ማውጣት አይችልም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ4-6 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ሃሳብ የሰነዘረባቸው ሶስቱ ርዕሶች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ሶስት ርዕሶች አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ምን ታያለህ?
4. በነዚሁ ቁጥሮች ላይ መንፈስ ቅዱስ፣ ኢየሱስና እግዚአብሄር አብ እያንዳንዳቸው ከምን ጋራ በመያያዝ እንደተነገሩ ተናገር፡፡ ይህንን ስትመለከት የምትማረው እውነት ትችላለህ?
5. በቁ7 መሰረት መንፈስ ቅዱስን መግለጥ የሚሰጠው ለማን ነው? መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ወይም ሥጦታዎች የሚሰጡት ምክንያትስ ለምንድነው?
6. ከቁ8-10 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስንመለከት አንድ ግልጽ ሆኖ የሚታየው እውነት ምንድነው?
7. ቁ11 የሥጦታዎቹ ባለቤት ማንነው ይላል? ወደ መንፈሳዊ ነገር ሳናመጣው ሥጦታ የሚለውን ሃሳብ አስመልክቶ የምታውቃቸውን እውነቶች ተነጋገሩባቸው፡፡
8. ቁ11 ሰጪው ስጦታውን ሲሰጥ አሰጣጡ በምን ዓይነት ነው? ከላይ ባየናቸው ቁጥሮች በተለይም በቁ7 መሰረት መንፈስ ቅዱስ ስጦታውን ሲሰጥ በምን መንገድ እንድንጠቀምበት ነው? ስጦታዎች ለግል ጥቅም ሲውሉ ገጥሞህ ያውቃል ወይ? ራስህንስ በዚያ መስመር ላይ አግኝተኸው ታውቃለህ? እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ስጦታን የሰጠህ ለራስህ መጠቀሚያ ሳይሆን ሌሎችን እንድትጠቅምበት ስለሆነ በጥንቃቄ ልታገለግልበት ስለሚገባህ ዘወትር ጥንቃቄ አድርግ!

# ጥናት ሃያ ሶስት 1ኛ ቆሮ 12፡12-21

የጥናት: እግዚአብሄር ራሱ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሰጠንን ቦታ በመያዝ እንደ አንድ ብልት የሚጠበቅብንን ሃላፊነት መወጣት እንጂ፣ ከሌሎች ብልቶች ጋራ ራሳችንን በማወዳደር ለዝቅተኛነት ስሜትም ሆነ ለትዕቢት ቀዳዳን መፍጠር እንደማይኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን እግዚአብሄር እንደወደደ እያንዳንዱን በየቦታው መድቧል፡፡ 1ኛ ቆሮ 12፡18

1. 1ኛ ቆሮ 12፡12-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ12 ክርስቶስን የሚያመሳስለው ከምን ጋራ ነው? ይህ ቁጥር  አንድን እውነት ለማስረዳት የተጠቀመባቸው ሁለት ገጽታዎች ምንና ምንድናቸው?
2. ቁ13ትን ስናነብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በተገናኘ በህይወታችን የተካሄዱት ሁለት ነገሮች ምንድናቸው? ይህ ክፍል በአንድ መንፈስ የተጠመቅንበት ምክንያት ለምንድነው ይላል?
3. በቁ13 ላይ የሰፈረው ሃሳብ በቁ12 ላይ ከተነገረው እውነት ጋራ የሚዛመድበትን መንገድ በራስ አማርኛ አስረዳ፡፡ ቁ13 በአካሉ ውስጥ ስለሚገቡት የሰዎች ዓይነትና ማንነት ምን ይነግረናል?
4. ቁ14-16 ላይ የሚነበበውን ሃሳብ በአንድ አጭር ዓረፍተ ነገር በመጠቅለል ተናገር ብትባል ምን ትላለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በአንተ አመለካከት ሌሎችን ለመሆን የምናሳየውን ፍላጎት የሚጠቁመን የትኛው አነጋገር ነው ትላለህ?
5. ቁ17-18ትን በማንበብ ሐዋርያው ሌሎችን ለመሆን የምናደርገውን ሙከራና ፍላጎት ትክክል አለመሆኑን ለማረም የተጠቀመባቸው ሁለት እውነቶች ምንና ምንድናቸው?
6. ቁ19-20 ባለው ክፍል የሐዋርያው ጥያቄ ምንድነው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ለሃሳቡ ማጠቃለያ በማድረግ የተጠቀመበት ዓረፍተ ነገር ምንድነው?
7. በቁ21 ውስጥ ጸሐፊው ሊፈታ የሚሞክረው ችግር በቁ15-20 ካነበብነው ችግር በምን ይለያል ትላለህ? ባለንበት ዘመን ስትመለከት ከእነዚህ ከሁለት ችግሮች የትኛው ጎልቶ ታየዋለህ?
8. በቁ18 ላይ የሰፈረውን እውነት በትክክል መረዳት እንዴት ነው እነዚህን ሁለት ዓይነት ችግሮች ለማሸነፍ የሚጠቅመው? በአካሉ ውስጥ እግዚአብሄር የሰጠህን ቦታ በመያዝ እንደብልት የሚጠበቅብህን ማድረግ እንጂ ራስህን ከሌላ ጋራ በማነጻጸር ለመኖር እንዳትሞክር በርታ፡፡

<u>ጥናት ሃያ አራት 1ኛ ቆሮ 12፡22-31</u>

የጥናት: እግዚአብሄር አማኞችን ሁሉ እንደ አካል እርሱ በሚፈልገው መንገድ ያገጣጠመ ስለሆነ መለያየት የሚያመጡትን ነገሮች ማስወገድ፣ ከዚያም አልፎ እርስ በእርስ መተሳሰብ ሃላፊነታችን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄር ግን የአካል ብልቶችን በአንድ ላይ አገጣጥሞ… ክብር ሰጥቷቸዋል፤ ይህንም ያደረገው በአካል ብልቶች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በእርሳቸው እኩል እንዲተሳሰቡ ነው፡፡›› 1ኛ ቆሮ 12፡24-25

1. 1ኛ ቆሮ 12፡22-31 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ22 ላይ የተሰነዘረው አነጋገር የትኛውን ሃሳብ ለመቃረን የቀረበ ሃሳብ ነው? በዚህ ክፍል ጳውሎስ ሊያስረዳን የፈለገው እውነት ምንድነው?
2. ቁ22-24 ባሉት ቁጥሮች ሐዋርያው የጠቀሳቸው ቢያንስ አራት ዓይነት ብልቶችን ዘርዝር፡፡ በተለይ ሁለቱን ሲጠቅሳቸው ‹‹የሚመስሉ›› በማለት ነው፤ ከዚህ አነጋገሩ የምንረዳው እውነት ምንድነው?
3. በነዚሁ ቁጥሮች አነጋገር መሰረት ክብርና እንክብካቤ ሊሰጥ የሚገባው ለነማን ነው? በቁ24 የአካል ብልቶችን ያገጣጠመ ማንነው ይላል? ‹‹አገጣጥሟል›› ሲልስ ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
4. ‹‹…ክብር ለሚጎድላቸው የበለጠ ክብር ሰጥቷቸዋል›› በማለት ሲናገር እናያለን፡፡ ቁ25 እግዚአብሄር ይህንን ስላደረገበት ምክንያት ጳውሎስ የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት ነገሮች በተግባር ላይ ሲውሉ ስለሚከሰቱት ሁለት ነገሮች በቁ26 ላይ ያሉትን ሃሳቦች ተናገር፡፡
5. በቁ28 ላይ የሰፈሩትን የስጦታ አይነቶች ዘርዝር፡፡ እነዚህን ሁሉ የስጦታዎች ዝርዝር ስንመለከት በቁ14 ላይ ለተነገረው እውነት ማረጋገጫ የሚሆንልን በምን መንገድ ነው?
6. ቁ11፣ ቁ18፣ ቁ28 ትን በማንበብ የስጦታዎችን አሰጣጥ አስመልክቶ ስለ እግዚአብሄር ተሳትፎ ምን ትረዳለህ? ቁ31 ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ የሚጠቁመን ሌላ አንድ እውነት ምንድነው?
7. ቁ29-30 ላይ ጸሐፊው የጠየቃቸውን ጥያቄዎች ዘርዝር፡፡ ዓውደ ምንባቡን በማየት፤ እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ? ለጥያቄዎቹስ የሚጠብቀው መልስ ምንድነው?
8. ዛሬ ያጠናነው ጥናት በመመርኮዝ ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ አመለካከት አለው የምትለው ምን አይነቱን አማኝ ነው? በቅዱሳን መሃል መለያየት እንዳይኖር ምን ያህል ጥረት ታደርጋለህ? ለሌሎች ወገኖች ማሰብና መተሳሰብስ ምን ያህል ትለማመዳለህ? መለያየት እንዳይከሰት መተሳሰብ ደግሞ እንዲኀለብት ዘወትር የምትተጋበት ነገር ይሁንልህ፡፡

# <u>ጥናት ሃያ አምስት 1ኛ ቆሮ 13፡1-13</u>

የጥናት ዓላማ: የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መታጀብ እጅግ ፍሬያማ ሊያደርጋቸው እንደሚችልና፤ እግዚአብሄር ያቀደላቸውን ግብ ለመምታት አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብናገር፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሻሻ ጸናጽል ነኝ፡፡›› 1ኛ ቆሮ 13፡1

1. 1ኛ ቆሮ 13፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 ላይ በልሳን እየተናገረ ፍቅር ግን የሌለውን ሰው በምንድነው የሚመስለው? ‹‹በሰዎችና በመላዕክት ልሳን…›› ሲል መላዕክትን በዚህ ውስጥ ማስገባት የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
2. በቁ1-3 ውስጥ የተጠቀሱትን ቢያንስ አምስት ዓይነት ስጦታዎች ዘርዝር፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ‹‹ፍቅር ግን ከሌለኝ›› የሚለው ሃረግ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል?
3. ልክ ‹‹ፍቅር ግን ከሌለኝ›› የሚለውን ሃረግ ከመጠቀሙ በፊት የሚገኙት ሶስት ቃላት ምን ምንድናቸው? ማናቸውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከእነዚህ ከሶስት ቃላት በአንደኛቸው ውስጥ ይጠቀለላል በሚለው አነጋገር ትስማማለህ ወይ? ለምን?
4. ቁ4-7 ላይ ስለ ፍቅር የተነገሩትን ነገሮች በየተራ አንድ በአንድ ዘርዝራቸው፡፡ ለምን ይመስልሃል ጳውሎስ የፍቅርን ምንነት በዚህ መልኩ ለመዘርዘር የፈለገው?
5. የቆሮንቶስ ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ከመንፈስ ፍሬ በየትኛው የበለጠጉ ናቸው ትላለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ ለምንድነው ይመስልሃል ፍቅር በክርስትና ህይወት ውስጥ ዋነኛና ማዕከላዊ ነገር ሆኖ ሊታይ የሚገባው?
6. በቁ8-10 ላይ ፍቅርን የሚያወዳድረው ከምን ጋራ ነው? እውቀት ስለሚሻርበት ምክንያት ይህ ክፍል የሚነግረን ነገር ምንድነው?
7. ቁ11-12 ሲነበብ፤ በተለይ ቁ11 ላይ በብዛት ተደጋግሞ የምናየው አንድ ቃል ምንድነው? ይህ ቃል በዚህ በአንድ ቁጥር ውስጥ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል? በቁ 12 ላይ ጊዜን የሚጠቁሙ ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው?
8. በተራ ቁጥር 7 ላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች መሰረት፤ ‹‹ልጅ›› የሚለውና ‹‹ጎልማሳነት›› የሚሉት ቃላት የሚወክሏቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ጳውሎስ በምዕራፍ 13 ውስጥ ለተናገረው ሁሉ ሃሳብ መጠቅለያ አድርጎ ተጠቅሞበታል የምትለው አንድ ጥቅስ የትኛው ነው?
9. ቁ1-3ትን መለስ ብለን ስናይ በልሳን መናገር፣ ትንቢት መናገር፣ ለድሆች መስጠትና የመሳሰሉት የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ አይጠቅሙም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነ ግን ታዲያ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሐዋርያው ምን ለማለት ነው የፈለገው? የጸጋ ሥጦታዎችና የመንፈስ ፍሬዎች እንደማይነጣጠሉ አስተውለህ ታውቃለህ ወይ? ከጌታ በነጻ የተቀበልከውን ስጦታ እንደሚገባ ፍሬያማ እንዲሆን ከፈለግህ የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ፍቅርን በህይወትህ ለማሳደግ ትጋ፡፡

# ጥናት ሃያ ስድስት 1ኛ ቆሮ 14፡1-12

የጥናት ዓላማ: እንደ ቤተ ክርስትያን ለመሰባሰባችን ዋነኛው የእግዚአብሄር ዓላማ እርስ በእርስ በመተናነጽ፣ በመበረታታትና በመጽናናት እግዚአብሄርን ማክበር መሆኑን ግንዛቤ ለማድረግ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት ለሰው ይናገራል፡፡ በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ቤተ ክርስትያንን ያንጻል፡፡›› 1ኛ ቆሮ 14፡3-4

1. 1ኛ ቆሮ 14፡1-12 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥር ላይ የተሰጡን ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? በተለይ አማኞች አጥብቀን እንድንፈልገው የተነገረን አንድ የስጦታ አይነት ምንድነው?
2. በቁ2-5 ላይ ጳውሎስ እያነጻጸረና እያወዳደረ የሚናገርላቸው ሁለት ስጦታዎች ምንና ምንድናቸው?
3. በቁ2 ላይ በልሳን ስለመናገር አስመልክቶ የተነገሩት እውነቶች ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ቁ3 ትንቢት መናገር ከሚያጠቃልላቸው ነገሮች በቁ3 ላይ የተዘረዘሩት ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ሃሳቦች ስታይ በአብዛኛው ትንቢት ብለን ከምናስበው ሃሳብ እንዴት እንደሚገናዘብልህ አስረዳ፡፡
4. በቁ4ት በማንበብ እነዚህን ሁለት ስጦታዎች የሚለያቸው አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? በቁ1 ላይ ትንቢትን አስመልክቶ የተናገረንን ሃሳብ በመጤን ከዚህ ቁጥር ጋራ ስናገናዝብ ልንደርስበት የምንችለው አንድ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ማሰሪያ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ?
5. ልሳንንና ትንቢትን አስመልክቶ ሐዋርያው ስላለው አመለካከት በቁ5 የምታያቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ ከላይ በተመለከትናቸው አምስት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ሊያስተምሩን የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ?
6. በቁ ላይ የጳውሎስ ጥያቄ ምን ነበረ? ‹‹ምን እጠቅማችኋለሁ›› ከሚለው ሃሳብ በመነሳት በልሳን መናገሩ ለቆሮንቶስ ሰዎች የማይጠቅምበትንና ሌሎቹ በዚህ ክፈል የተጠቀሱት ስጦታዎች ግን ለነዚህ ሰዎች ጠቃሚ የሚሆኑበት ምክንያት ለምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
7. ቁ7-9 ላይ ጸሃፊው ሃሳቡን ለማስረዳት የተጠቀመው ምንን ምሳሌ በማድረግ ነው? በዚህ ምሳሌ መሰረት የሙዚቃ መሳሪያው ጠቃሚና ትርጉም ያለው እንዲሆን ካስፈለገ ምን መሆን አለበት ይለናል? ‹‹እናንተም እንደዚሁ›› በማለት ከሙዚቃ መሳሪያዎቹ እንድንቀስም የፈለገውን በራስህ ቋንቋ አስረዳ፡፡
8. ቁ10-12ትን ስናነብ ጳውሎስ ሌላ ሃሳቡን ሊያስተላልፍ የተጠቀመበት ምሳሌ ምንድነው? በዚህ ምሳሌ ውስጥ ያለውን ሃሳብ በራስህ ቋንቋ በአጭሩ ተናገረው፡፡ በቁ12 ላይ የጳውሎስ ምክር ምንድነው?
9. አንድ አማኝ ቁ12 ትንና ቁ3-4 ትን በአንድነት ተመልክቶ ሊደርስበት የሚችለው ማጠቃለያ ሀሳብ ምንድነው ትላለህ? ወደ ቤተ ክርስትያን ስትሄድ በወገኖች ስጦታ ለመታነጽ፣ ለመበረታታትና ለመጽናናት ምን ያህል ልብህ የተዘጋጀ ነው? አንተም በጉባኤ መሃል ስጦታህን ስትለማመድ በቁ3 ላይ የተነገሩትን ጥቅሞች ይሰጣል ወይ ራስህን በመጠየቅ ተጠቀምበት፡፡

# ጥናት ሃያ ስባት 1ኛ ቆሮ 14፡13-26

የጥናት ዓላማ:- አማኞችን የማያንጽ ከመሆኑም አልፎ በስብሰባችን የተገኙትን ያላመኑ ሰዎች ደግሞ አብደዋል ሊያሰኝ የሚችል በመሆኑ፤ ድምጻችንን ከፍ አድርገን በልሳን እንድንናገር ወይም እንድንጸልይ የሚደረገው መገፋፋት ከመንፈሳዊነት ይልቅ ሕጻንነትን እንደሚያመለክት ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ:- ‹‹ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሄርን አመሰግናለሁ፡፡ ነገር ግን በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተማር…ወንድሞች ሆይ በአስተሳሰባችሁ ህጻናት አትሁኑ፤›› 1ኛ ቆሮ 14፡18-20

1. 1ኛ ቆሮ 14፡13-26 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ13 ላይ በልሳን የሚናገር ሰው ምን እንዲያደርግ ነው የተመከረው? ጳውሎስ ለምን ይመስልሃል ለዚህ ነገር እንዲጸልይ የሚመከረው?
2. ቁ14-5ትን ስናነብ፤ በልሳን በምንናገርበት ሰዓት በውስጣችን ስለሚካሄደው ነገር ይህ ክፍል ምን ይነግረናል? በመንፈስ ስለ መጸለይና በዓዕምሮ ስለ መጸለይ ከነዚህ ቁጥሮች የምትረዳውን ተናገር፡፡
3. ለምንድነው ጳውሎስ በአዕምሮ መጸለይንና በአዕምሮ ደግሞ መዘመርን አስፈላጊ ነገር ሆኖ የሚያየው? ቁ16-17 ይነበብ፡፡ ቁ16 ‹‹እንግዳ የሆነ ሰው››፣ ቁ17 ‹‹ሌላው ሰው››፣ ቁ19 ‹‹ሌሎችን›› የሚሉት አነጋገሮች ስለ ስጦታዎቻችን የሚነግሩን ነገር ምንድነው?
4. ጳውሎስ በቁ18-19 ላይ ራሱን ከቆሮንቶስ አማኞች ጋራ ያወዳደረው ምንን አስመልክቶ ነው? ጳውሎስ  በዚህ ስፍራ እግዚአብሄርን የሚያመሰግነው ከእነርሱ በልጦ በመገኘቱ ይመስልሃል ወይስ ከበስተኋላ ሌላ ምክንያት ታያለህ?
5. በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ጸሐፊው ሌላ ሲያወዳድራቸው የሚታዩት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የትኛው ይበልጣል ነው የሚለው? ለምን ይመስልሃል አንዱ ከሌላው በልጦ መገኘት የቻለው?
6. ቁ20-21 ላይ ‹‹በአስተሳሰባችሁ ሕጻናት አትሁኑ›› ሲል በአውደ ምንባቡ መሰረት ጳውሎስ የሚናገረው ስለ የትኛው ዓይነት አስተሳሰብ ነው?
7. ቁ23-25 ላይ ከዚህ በፊት ካየነው ምክንያት በተጨማሪ፤ በጉባኤ መሃል በልሳን መናገርን የማያደፋፍር በተጨማሪ ሌላ ምን ምክንያት ታያለህ? እነኚህ ቁጥሮች የሚያበረታቱት ከልሳን ይልቅ ምንን ነው?
8. ዛሬ ባጠናነው ምንባብ ውስጥ በቤተ ክርስትያን ውስጥ የማይተረጎም ልሳንን ከመናገር እንድንቆጠብ ሊያደርጉን የሙችሉ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች ተናገር፡፡ ለምን ይመስልሃል ቤተ ክርስትያን ይህንን ሁሉ እያወቀች በዚህ እውነት ለመመላለስ ስትቸገር የሚታየው? እውነቱን ከመንፈስ ቅዱስ ከተማርክ፤ አስቸጋሪም ቢሆን እንኳን ለእውነት መቆምህን አትተው፡፡

# ጥናት ሃያ ስምንት 1ኛ ቆሮ 14፡27-40

የጥናት ዓላማ: በልሳን የመናገር ስጦታ ዛሬም በእኛ ዘመን እግዚአብሄር ለቤተ ክርስትያን እየሰጠ ያለው ስጦታ መሆኑንና፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደማንኛውም ስጦታ በአግባብና በሥርዓት መጠቀም እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፤ በልሳን መናገርንም አትከልክሉ፤ ነገር ግን ሁሉም በአግባብና በሥርዓት ይሁን፡፡›› 1ኛ ቆሮ 14፡39-40

1. 1ኛ ቆሮ 14፡27-40 በአንድነት ይነበብ፡፡ የዛሬውን ምንባብ ስትመለከት ክፍሉ ያተኮረባቸው ሁለቱ የጸጋ ሥጦታዎች ምንና ምንድናቸው? በቁ26 ላይ የምታያቸውን ስጦታዎች ዘርዝር፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ሊያስገኙ ስለሚጠበቅባቸው ውጤት ክፍሉ ምን ይጠቁመናል?
2. ቁ27-28 ላይ ስናነብ በተለይም ቁ27 ሐዋርያው የሚሰጣቸው ትዕዛዝ ምንድነው? በልሳን የተነገረውን የሚተረጉም በማይኖርበት ጊዜ፤ ለልሳን ተናጋሪው የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?
3. ‹‹በምትሰበሰቡበት ጊዜ››፣ ‹‹በጉባኤ›› የሚሉት አነጋገሮች ይህ ትዕዛዝ ተፈጻሚ ስለሚሆንበት ሥፍራ ምን ያስረዳናል? ቁ28 ትን ስትመለከት በጉባኤ መሃል ስንሰበሰብ የማይተረጎም ልሳን መናገርን ከልክሎናል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. ቁ29-33 ያሉት ሶስት ቁጥሮች ትኩረት ያደረጉት በየትኛው ስጦታ ላይ ነው? ቁ27 ትንና 29 ስታነጻጽር የምታየውን ተመሳሳይነትና ልዩነት አብራራ፡፡
5. ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች በየተራ እንዲናገሩ ስለመደንገጉ ምክንያት ሆነው የሚታዩህን ነገሮች ከክፍሉ ውስጥ እያወጣህ ተናገር፡፡
6. በቁ37-38 ላይ ሃዋርያው የሚናገረውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ? ‹‹የማያውቅ ቢሆን ግን እርሱ አይታወቅ›› ሲልስ ምን ማለቱ ይመስልሃል?
7. ቁ39-40ን ስታነብ ከቁ1 ጋራ የሚመሳሰልበትን ምን ሃሳብ ታያለህ? ለምንድነው በአንተ አመለካከት ሐዋርያው ይህንን ሃሳብ ለመደጋገም የፈለገው?
8. በነዚሁ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ልሳንን አስመልክቶ የተነገሩትን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡ በቁ28 ላይ ያየነው ሃሳብ በምን መንገድ ከቁ39-40 ጋራ በምን መንገድ ታያይዘዋለህ? በልሳን እንዳንናገር አልተከለከልንም፤ ሆኖም የማይተረጎም ሲሆን እግዚአብሄር እንጂ ሰዎች እንደሚሰሙት አድርጎ መናገር አማኞችን የማያንጽ፤ ያላመኑትን ደግሞ ሊያስናክል ስለሚችል ስጦታችንን በሥርዓትና በአግባብ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ 1ኛ ቆሮ 15፡1-11

የጥናት ዓላማ:- የምንሰብከው ወንጌል ሐዋርያቱ የሰበኩት ዓይነት እንዲሆን ካስፈለገ፡ ክርስቶስ ስለ ሐጥያታችን እንደሞተ፣ እንደተቀበረና፣ በሶስተኛው ቀን እንደተነሳ የሚናገር ስብከት መሆን እንደሚኖርበት ለማስገንዘብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ክርስቶስ ስለ ሃጥያታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻህፍት እንደ ተጻፈውም በሶስተኛው ቀን ተነሳ…እንግዲህ እኔም ሆንኩ እነርሱ የምንሰብከው ይህንኑ ነው›› 1ኛ ቆሮ 15፡3-4፣ 11

1. 1ኛ ቆሮ 15፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2 ላይ ወንጌሉ ከቆሮንቶስ አማኞች ጋራ ስላለው ግንኙነት የሚጠቅሳቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዚህ ክፍል ሰዎቹ ትክክለኛ ደህንነት ማግኘታቸው ስለሚረጋገጥበት መንገድ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
2. በቁ2 ላይ ያለውን ሃሳብ በዮሐ 8፡31-32 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገረው ንግግር ጋራ እንዴት እንደሚመሳሰልና እንደሚደጋገፉ አስረዳ፡፡
3. ቁ3 ‹‹የተቀበልኩትን›› ‹‹ለእናንተ አስተላልፌአለሁ›› የሚሉት አነጋገሮች ስለ ወንጌል አካሄድ ምን የሚያስተምረን ነገር አለ ትላለህ? በዚህ ቁጥር ላይ ጳውሎስ ለወንጌል ስለሚሰጠው ሥፍራ ምን ትረዳለህ? ለአንተስ ወንጌል ከሁሉ ነገር በላይ ሆኖ ይታይሃል ወይ?
4. በቁ3-4 መሰረት ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች ካስተላለፋቸው የወንጌል እውነት መሃል የሚጠቅሳቸውን ዘርዝር፡፡
5. በዚህ ምንባብ ውስጥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሳት የዓይን ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ስንት ሰዎች ታያለህ? ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት ቤተ ክርስትያንን በማሳደዱ ስለ ተሰማው ስሜት የሚነግረን የትኛው ቁጥር ነው?
6. በቀድሞው በጳውሎስ ህይወቱና በአሁኑ ህይወቱ መሃል የምታየው ልዩነት ምንድነው? ለቀድሞው ህይወቱ ጳውሎስ ራሱን ተጠያቂ ሲያደርግ፤ ዛሬ ላለበት ህይወት ወይም የክብር ቦታስ ተጠሪ የሚያደርገው ማንን ነው? ዛሬ በህይወትህ በዝቶ ላለው በጎ ነገር ሁሉ ምን ያህል ለእግዚአብሄር ጸጋ ሥፍራውን ትሰጣለህ?
7. ቁ10 ላይ ‹‹ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋ ከንቱ አልሆነም›› ሲል ምን ትረዳለህ? በዚሁ ቁጥር ላይ ‹‹በእግዚአብሄር ጸጋ…ሆኛለሁ›› ‹‹በተሰጠኝ ጸጋ…በትጋት ሰርቻለሁ›› የሚሉትን አነጋገሮች ስትመለከት፤ የእግዚአብሔር ጸጋ በአማኝ ህይወት የሚሰራባቸው ሁለት የተለያዩ መንገዶች ምንና ምንድናቸው?
8. በቁ11 ላይ ሐዋርያው ‹‹እኔም ሆንሁ እነሱ የምንሰብከው ይህንኑ ነው›› ሲል ወደ የትኛው ሃሳብ ነው እየጠቆመ ያለው? ለሰዎች ወንጌልን ስትናገር የክርስቶስ ሞት፣ ቀብርና ትንሳኤውን ዋነኛ የምስክርነትህ ማዕከላዊ ሃሳብ ነው ወይ? የጌታን ሞትና ትንሳኤ ያላካተተ ምስክርነት የተሟላ ወንጌል ሊሆን ስለማይችል ሁሌ ለማስታወስ ሞክር፡፡

# ጥናት ሰላሳ 1ኛ ቆሮ 15፡12-34

የጥናት ዓላማ:- ትንሳኤ መኖሩን ማመናችን፤ በህይወታችን በሚገጥሙን ማናቸውም ሁኔታዎች ሳንበገር፤ በቆራጥነትና በእምነት መወጣት የምንችልበትን ጽናት የሚሰጠን እውነተኛ ሃይል እንደሆነ

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…እኛስ ብንሆን ዘወትር ለአደጋ የምንጋለጠው ለምንድነው? ወንድሞች ሆይ፤ እኔ በየቀኑ እሞታሁ…ከአራዊት ጋራ የታገልኩት ለሰው አስተያየት ብቻ ከሆነ ትርፌ ምንድነው?›› 1ኛ ቆሮ 15፡30-32

1. 1ኛ ቆሮ 15፡12-34 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ12-13 ላይ ሊነጣጠሉ እንደማይችሉ አድርጎ የሚያቀርባቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ቁ14-15 ትን ስታነብ በክርስቶስ ትንሳዔ ላይ የተንጠለጠሉት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝራቸው፡፡
2. በቁ12-20 ላይ ከምታየው የሃዋርያው አነጋገር ስለትንሳኤ ምን ትረዳለህ? ከላይ ለዘረዘራቸው ሃሳቦች በሙሉ የጳውሎስ መደምደሚያ ሃሳቡ ምን ነበረ?
3. በቁ21-22 ከምናነበው ሃሳብ ስለሞትና ትንሳኤ መገንዘብ የምንችለው እውነት ምንድነው?
4. ቁ23-24 ላይ ስለትንሳኤ ቅደም ተከተል ጳውሎስ የሚናገረው ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች መሰረት ፍጻሜ የሚሆነው መቼ ነው?
5. ቁ26-28 ላይ ሞትን እንድንመለከት የሚፈልግበት መንገድ ምን ይመስላል? በነዚህ ቁጥሮች ግራ ሊያጋባ የሚችለውና ጳውሎስም ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥ ያስፈለገው ነገር ምን ነበረ? ማስተካከያው ሃሳብ ምን የሚል ነበረ?
6. 1ኛ ቆሮ 5፡11 ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ከምን ዓይነት ሰው እንዲርቁ ነው የሚያዛቸው? በዛሬው ጥናት ቁ32-33 ላይስ ጓደኛ እንዳይሆኑ ማለትም እንዲርቁ የሚጠየቁት ከምን ዓይነት ሰው ነው?
7. ቁ30-32ትን ስታነብ ጳውሎስ ስለትንሳኤ ያለው ጠንካራ አመለካከት እለት በእለት በሚኖረው ኑሮው ላይ ሲከሰት የምታየው በምን መንገድ ነው? አንተስ ስለትንሳኤ ያለህ የአመለካከትህ ጥንካሬ መከራና ስደትን ለመቋቋም በህይወትህ የሚጫወተው ሚና ምንድነው?

# ጥናት ሰላሳ አንድ 1ኛ ቆሮ 15፡35-58

የጥናት ዓላማ:- ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳ ያመንና፤ ከዚያም አልፎ የትንሳኤ ተስፋ ያለን እኛ፤ በእምነታችን ጸንተን ለመንቆም፣ በነገሮች ሁሉ እንዳድናወጥና፣ ለጌታ የምንደክመው ድካማችን ሁሉ ከንቱ እንዳልሆነ በመረዳት የትንሳኤው ተስፋ ለጌታ ሥራ ዘወትር እንድንተጋ የሚያደርገን ትልቅ ማበረታቻ ሊሆን እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ:- ‹‹ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሄር ምሥጋና ይሁን፡፡ ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንጻችኁ ቁሙ፣ በምንም ነገር አትናወጡ፣ ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፡፡›› 1ኛ ቆሮ 15፡57-58

1. 1ኛ ቆሮ 15፡35-58 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ35-38 ላይ ጳውሎስ መልስ ሊሰጣቸው የሚሞክራቸው ሰዎች ምን ዓይነት ጥያቄ ነው ያላቸው? መልሱን ለመስጠት እየተጠቀመበት ያለው የምንን ምሳሌ ነው? እንደዚህ አይነት ጥያቄ ለምንድነው በተለይ እነዚህን ሰዎች ‹‹አንተ ሞኝ›› ሊያሰኝ የሚችለው?
2. በቁ39 ላይ ሥጋ ሁሉ አንድ አለመሆኑን ለማስረዳት ስንት የሥጋ ዓይነቶች ተጠቅሰዋል? ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡በቁ40-41 ላይ በብዛት የሚታይ አንድ ቃል ምንድነው? ስንቴ ተጠቅሶ ይገኛል?
3. ቁ40-41ድን በማንበብ ሰማያዊ አካልን ከምድራዊ አካል የሚለየውን ነገር በአንድ ቃል አጠቃልል ብትባል ምን ትላለህ? በቁ42-44 ላይ የሚዘሩበት አራት መንገዶች ምን ምንድናቸው? አራቱስ የሚነሱባቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው?
4. በቁ45-49 ላይ ስንት ዓይነት አዳም ትመለከታለህ? በሁለቱ አዳሞች መሃል የምታያቸውን ልዩነቶች ሁሉ ዘርዝር፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ አዳሞች ጋራ ስለሚኖረን ግንኙነቶችስ ክፍሉ ምን ያረጋግጥልናል?
5. ሊሆኑ እንደማይችሉ አስረግጦ ጳውሎስ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች በቁ50 ላይ የትኞቹ ናቸው? በቁ51 መሰረት ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የሚነግራቸው ምስጢር ምንድነው? እነዚህ ነገሮች መቼ ይሆናሉ?
6. መቼ ነው ሞት በድል መዋጡ የሚረጋገጠው? ከ54-57 ያለውን ስናነብ ሞትን ከሚያህል ትልቅ ባላጋራ ነጻ እንድንወጣና እንድናሸንፍ ያስቻለን ምንድነው ይላል?
7. ቁ58 የጀመረው ምን በሚል ቃል ነው? ይህ ቃል ሁለት ሃሳቦችን የሚያያይዝ ቃል ነው፤ በዚህ ሊያያይዝ የሚሞክረው ከየትኛው ሃሳብ ጋራ ይመስልሃል?
8. የሞት ድል መነሳትና የአማኞች በሞት ላይ ድልን መቀዳጀት፤ በቁ58 ላይ ሊያስከትል የሚገባቸው ሆኖ ጳውሎስ የሚጠቅሳቸው ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? በመጨረሻ ሞት ድል በመነሳት መዋጡና ለአንተም ትንሳኤ እንደሚጠብቅህ መረዳትህ በጌታ ሥራ ላይ ትጋት እንድታሳይ ምን ያህል በህይወትህ አስተዋጽዖ አድርጎ ታያለህ?

# <u>ጥናት ሰላሳ ሁለት 1ኛ ቆሮ 16፡1-24</u>

የጥናት ዓላማ:- በጌታ ቤት ረጅም ዘመን ማሳለፋችን ከሌሎች በላይ መሆናችንን የምናረጋግጥበት ልዩ ሜዳልያ ሳይሆን፤ በቤቱ ያካበትናቸውን መልካም ልምዶች ቅዱሳን በወንጌል ጸንተው እንዲቆሙ የምናገለግልበት መሳሪያ ሊሆነን እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የእስጢፋኖስ ቤተ ሰዎች በአካይያ የመጀመሪያዎቹ አማኞች እንደሆኑና ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደሰጡ ታውቃላችሁ፡፡›› 1ኛ ቆሮ 16፡15

1. 1ኛ ቆሮ 16፡1-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ በተለይም ቁ2ትን ስትመለከት የገንዘብ መዋጮን አስመልክቶ ልንማር የምንችላቸውን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ለቆሮንቶስ ሰዎች የሰጠው መመሪያ ለእነርሱ ብቻ የሚሰራ አድርገው እንዳናስብ የሚረዳን ሃሳብ ምንድነው?
2. የተሰበሰበው ገንዘብ በሚያስፈልገው ቦታ ላይ እንዲውል በዚህ ክፍል ጳውሎስ ሊወስድ ስላለው እርምጃ ምን ትመለከታለህ?
3. በቁ5-9 ላይ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች እየገለጠላቸው ያለውን ነገር በአንድ ወይም በሁለት ቃላት ብቻ ግለጽ ብትባል ምን ትላለህ? ያዕ 4፡13-16 ያለው ሃሳብ ከዚህ ክፍል ጋራ በምን ይመሳሰላል? ያንተስ እቅድህን ስታቅድ ምን ያህል በእግዚአብሄር ላይ ትተማመናለህ?
4. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስትመለከት፤ ጳውሎስ ለምንድነው በኤፌሶን ከተማ መቆየት የወሰነው? እንደሌሎቻችን ቢሆን ውሳኔውን ሊያሳጥፈው የሚችል ምን ነገር ትመለከታለህ? ከዚህ ውሳኔው ልንማር የምንችለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
5. በቁ10-11 ላይ ለቆሮንቶስ አማኞች ጢሞቲዎስን አስመልክቶ የተሰጧቸው ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ሁለቱን ሃሳቦች የሚመስሉ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ለራሱ የተናገራቸውና ትዝ የሚሉህን ለወገኖች አካፍል፡፡
6. በቁ17-18 ላይ ጳውሎስን ደስ ያሰኘው ነገር ምን ነበረ? እነዚህ ሰዎች ሐዋርያውን ደስ ለማሰኘት ያደረጉት ነገር ምንድነው? ፊሊ 4፡16-17 ጋራ በማስተያየት ስነነበው፤ የጳውሎስ ደስታ ከችግሩ ነጻ ስላወጡት ይመስልሃል ወይ? አስረዳ፡፡
7. በተለይ ቁ18 ከምንመለከተው፤ ስለ እነዚህ ሶስት ሰዎች የጳውሎስ ምስክርነት ምን ይመስላል? ስለ ሰዎቹ ከመመስከር አልፎ፤ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን አስመልክቶ ለቤተክርስትያን የሚመክረው ምክር ምንድነው? የስንቶች መንፈስ በአንተ/በአንቺ አርፏል?
8. ቁ15-16 ላይ እስጢፋኖስ ስለተባለው ሰው ቤተ ሰዎች የሚነግረን ሁለት እውነቶች ምንና ምንድናቸው? በቁ16 ላይ ጳውሎስ አንባቢዎቹን የሚለምናቸው ምንድነው? ለምን? በእግዚአብሄር ቤት ያሳለፍከው ጊዜ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ምን ያህል ቅዱሳንን በማገልገል ትጠቀምበታለህ? በቤተ ክርስትያን አመታት ማሳለፍህን ሳይሆን ቅዱሳንን እያገለገልኩ ነው ወይ ብለህ ራስህን ልትጠይቅ ይገባሃል፡፡